ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ–ሙስና ቅጽ 1 ቁጥር 10 ሚያዝያ 30/2015 ዓ.ም

## ሀገራዊ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የ9 ወር አፈፃፀም የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተገኙበት ተገመገመ

ሀገራዊ የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የ9 ወር አፈፃፀም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና አባላት እንዲሁም የክልል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች በተገኙበት ተገምግሟል፡፡

የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ በመክፈቻ ንግግራቸው የሙስናና ብልሹ አሰራር ጉዳይ ሀገር የማስቀጠልና የህግ የበላይነት የማረጋገጥ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ሁሉም አካላት በቅንጅት መስራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የትውልድ የስነ-ምግባር ግንባታ ለፀረ-ሙስና ትግል ትልቅ ሚና ያለው በመሆኑ የስነ-ምግባር ግንባታውን አጠናክረን ማስቀጠል አለብን ብለዋል።

ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ አክለውም የሀብት ምዝገባ ማካሄድ ለፀረ-ሙስና ትግሉ አይነተኛ ሚና ያለው በመሆኑ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሀብት ምዝገባውን አጠናክራችሁ መስራት ይኖርባችኋል ብለዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ እውነቱ አለነ መንግስት ሙስና የሀገሪቱ ብሔራዊ የደህንነት ስጋት እንዳይሆን በየደረጃው የተለያዩ የፀረ-ሙስና ኮሚቴዎችን በማደራጀት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በትውልድ የስነምግባር ግንባታ ላይ ትኩረት በማድረግ የሙስና ችግር ከመሰረቱ ለመቅረፍ፥ የሃይማኖት ተቋማት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በስነ-ምግባር ግንባታ ላይ በሙሉ አቅማቸው መስራት እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር-ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢ አቶ አዝመራ አንደሞ በበኩላቸው፥ በዘለቄታው የሙስናን ችግር ለመፍታት ከእኛ ምን ይጠበቃል ብለን በመነሳትና አዋጆችን እና መመሪያዎችን በደንብ በማዘጋጀት ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት ይኖርብናል ብለዋል።







የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ዘርፍ ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው በመንግሥት ከሚበጀተው በጀት 70% ለግዥ አገልግሎት የሚውል በመሆኑ፥ ዘርፉን መፈተሽ ያስፈልጋል። አገልግሎት አሰጣጣችን ከሰው ንክኪ ነፃ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አሰራራችን ወደ ድጂታል በመቀየር ተቀናጅተን መስራት አለብን ብለዋል።

የፌደራል የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነ-ምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ወዶ አጦ በበኩላቸው የስነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጠንክሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል መንግስትና የምክርቤት አባላት እንዲያግዙ ገልፀው፥ ሙስናን ለመታገል መንግስት ሜዳውን ስላመቻቸልን በቅንጅት በመስራት ውጤታማ ስራ ማከናወን ይኖርብናል ብለዋል።

የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች 6ኛ የጋራ የትሥሥር ጉባኤ አባላት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና አባላት እንዲሁም የኮሚሽኑ የስራ ክፍል ኃላፊዎች በተገኙበት 9 ወራት መደበኛ ተግባራት እና የፀረ-ሙስና ኮሚቴው ያከናወኗቸውን ስራ እንዲሁም ሀገራዊ የስነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ፖሊሲ ዝግጅት መነሻ ሰነድ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበታል።

200 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እየታየ ነው

ገጽ 2

በሲዳማ ክልል በሙስና የተጠረጠሩ ግለሰቦችን የመለየት ስራ እየተከናወነ ነው

ገጽ 4



## በኦሮሚያ ክልል በሙስና በተጠረጠሩ 1 ሺህ 322 ግለሰቦች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተላለፈል

በኦሮሚያ ክልል በሙስና የተጠረጠሩ 4 ሺህ 80 ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር በማዋል 1 ሺህ 322 ግለሰቦች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ መተላለፉን የክልሉ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ገለጸ፡፡

በኦሮሚያ ክልል ሙስናን ለመከላከል የተቋቋመው የፀረ ሙስና ኮሚቴ የስራ ክንውኑን አስመልክቶ በዛሬው ዕለት መግለጫ ሰጥቷል።

ኮሚቴው በመግለጫው፥ ከሕዝቡ የቀረቡ 1 ሺህ 495 ጥቆማዎች በመመርመርና 642 የክስ መዝገቦችን በማደራጀት 1 ሺህ 322 ግለሰቦች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲተላለፍ ማድረጉን አንስቷል፡፡

በጥፋተኝነት ውሳኔውም ግለሰቦቹ ከ1 ዓመት እስከ 20 ዓመት በሚደርስ እስራት እንዲቀጡ መደረጉን ፋና ዘግቧል፡፡

# በዓለም ባንክ ትብብር በሚተገበሩ የልማት ፕሮጀክቶች በተከናወኑ
## የፀረ-ሙስና ስራዎች ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተካሄደ

በሀገሪቱ በዓለም ባንክ ትብብር በሚከናወኑ ሰባት የልማት ፕሮጀክቶች ከሙስና እና2 ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመተግበራቸው የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በማስመልከት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢዎች፣ የዘርፉ ተቋማት ኃላፊዎች፣ የክልል ሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽነሮች፣ የፕሮጀክቶች የክልል እና የፌደራል አስተባባሪዎች እና የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት ሚያዝ በአዳማ ከተማ የውይይት መድረክ ተካሂዷል::

ኮሚሽኑ የማረጋገጫ ሪፖርት የሚያደርግባቸው በአለም ባንክ ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በትምህርት ዘርፍ General Education Quality Improvement Program for Equity (GEQIP-E)፣ በግብርና ዘርፍ Climate Action through Landscape Management (CALM)፣ በ2ውሃና ኢነርጂ ዘርፍ (ELEAP)፣ በኢንዱስትሪ ዘርፍ (Economic Opportunity)፣ በከተማ እና መሰረተ ልማት ዘርፍ Urban Institutional and Infrastructure Development Program (UIDP)፣ በጤና ዘርፍ Health Sustainable Development Program (HSDP) እንዲሁም ፋይናንስ ዘርፍ Enhancing Shared Prosperity Through Equitable Services (ESPES) ፕሮጀክቶች ናቸው::

በመድረኩ የተገኙት የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) ፕሮጀክቶቹን በሚመለከት በዓመት ሁለት ጊዜ የፀረ-ሙስና ተግባራትን በማከናወን ለዓለም ባንክ ሪፖርት እንደሚደረግ ጠቅሰው መድረኩ በመጀመሪያው ግማሽ አመት በዚሁ ዙሪያ ስለተከናወኑ ተግባራት ከባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ





ለማድረግ መሆኑን ተናግረዋል::

በፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ለማረም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የክትትል ስራዎችን ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል::

ፕሮጀክቶቹ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ከ3.4 ቢሊዮን ዶላር በላይ በትብብር የሚተገበሩ ሲሆን፥ ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ እንዲተገበሩ እና የታሰበው አላማ እንዲሳካ የሚመለከታቸው ተቋማት ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል ብለዋል::



# 200 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እየታየ ነው

በአዲስ አበባ የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ 200 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን የከተማ አስተዳደሩ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ።

ግለሰቦቹ በተለያየ ደረጃ በቀረቡ በርካታ ጥቆማዎች ላይ ምርመራ በማድረግ በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለው ጉዳያቸው እየታየ መሆኑን የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ገልጸዋል።

ኮሚቴው በእስከአሁኑ እንቅስቃሴው ከ90 በላይ የምርመራና የክስ መዝገቦችን ማደራጀቱንም ጠቁመዋል፡፡

ለሙስና ተጋጭ በሆኑ መሬት፣ ኮንስትራክሽን፣ የግዥ ስርዓት፣ የታክስ፣ የጤና፣ የትምህርት ዘርፎች ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን እና የተጋላጭነት መጠንን የሚቀንስ አሰራር እየተዘረጋ ነው ብለዋል፡፡

ጥቆማ የሚቀበል፣ መረጃ የሚያሰባስብ፣ ምርመራና ጥናት የሚያካሂድ ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሞ የልየታ ሥራ ማከናወኑንም ነው ኮሚሽነሩ ለኢዜአ የተናገሩት፡፡

የፀረ ሙስና ኮሚቴው ጥቆማ የማሰባሰብ ሂደቱን እንደጀመረ የማህበረሰቡ ተሳትፎ አነስተኛ እንደነበር አስታውሰው፥ በተጠርጣሪዎች ላይ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ተከትሎ የህብረተሰቡ የጥቆማ ተሳትፎ እየጨመረ መምጣቱን አንስተዋል።

ለአብነትም በአንድ ሳምንት ብቻ 500 ያህል ጥቆማዎች ለኮሚሽኑ የቀረቡ ሲሆን፥ ይህም ህብረተሰቡ ሙስናን የመታገል ጽኑ ፍላጎት እንዳለው ያሳየ በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል ብለዋል፡፡

በተያያዘ መረጃ የማህበረሰብ አንቂዎች ዜጎች ሙስናን በመታገል በኩል ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በመስራት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የአዲስ አበባ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናን በመከላከል፣ በማጋለጥና ተጠያቂነትን በማስፈን በኩል የማህበረሰብ አንቂዎችን ሚና ለማጎልበት በተዘጋጀ መድረክ ላይ ጥሪ አቀረበ፡፡

የአዲስ አበባ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ በዚሁ ጊዜ እንደገለፁት ሙስና አይነቱን እየቀያየረ የሚፈጸም ወንጀል በመሆኑ የጸረ-ሙስና ትግሉ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡

ከዚህ አኳያ የማህበረሰብ አንቂዎች ኅብረተሰቡ በጸረ-ሙስና ትግሉ ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ የበኩላቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል ብለዋል፡፡

ሙስናን ለመከላከልና ተጠያቂነት ለማስፈን መንግስት ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሰራ መሆኑንም ጨምረው



ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ሙስና በህዝብና በመንግስት ላይ እያደረሰ ካለው የኢኮኖሚ ጫና ባለፈ የማህበረሰቡን መልካም እሴት እየሸረሸረ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት፡፡

በመሆኑም የማህበረሰብ አንቂዎች በትክክለኛና ተአማኒ መረጃ ላይ ተመስርተው ኅብረተሰቡ በጉዳዩ ላይ ያለው ንቃተ ህሊና እንዲያድግ ሊሰሩ ይገባል ብለዋል፡፡

የውይይቱ ተሳታፊዎች መንግስት ሙስናን ለመቀነስ እያደረገ ያለው ተግባር የሚበረታታ መሆኑን ገልጸው ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

በዋናነት ማህበረሰቡን ለማንቃት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸው መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸውም ጠይቀዋል።

ሙስና በአገርና በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት መገንዘብና ማጤን ያስፈልጋል ያሉት ደግሞ የአዲስ አበባ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ ናቸው።

ኮሚሽኑ አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰብ አንቂዎች የህግ ከለላ እንዲያገኙ ለማድረግ በኃላፊነት እንደሚሰራ ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ መሰል ውይይቶችን ከመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከአገር ሽማግሌዎች፣ ከማህበረሰብ ተወካዮችና ከወጣቶች ጋር እንደሚያካሂድም ተገልጿል።





# የተቋማት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ሚናቸውን በተገቢው ሊወጡ ይገባል

## - ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

በፀረ-ሙስና ኮሚቴ የስራ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከፌደራል ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎች እና የልማት ድርጅቶች የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊዎች በተገኙበት ውይይት ተካሂዷል።



በመድረኩ የተገኙት የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር እና የብሔራዊ ኮሚቴ አባል ክቡር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) እንደገለፁት በርካታ የሙስና ፍሬ ሀሳብ ያላቸውን ጥቆማዎች እየመጡ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ የህዝቡን ተሳትፎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱን ያሳያል ብለዋል።

በዚህ እረገድ ከተቋማት ሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች የሚቀርቡ ጥቆማዎች አነስተኛ በመሆናቸው በቀጣይ ሚናቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

መንግስት ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆኑን በመረዳት የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች መረጃና ማስረጃን መሰረት በማድረግ ለብሔራዊ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ጥቆማ ማቅረብ ይኖርባችኋል ብለዋል፡፡

በቀጣይ መሬት፣ ፋይናንስ፣ ፍቃድ አሰጣጥ እና ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ላይ ትኩረት በማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በተቋማት ላይ ያሉ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ትግል የሚያደርጉ እንዳሉ ሁሉ ከሌቦች ጋር በመሆን ሙስናውን የሚያሳልጡ መኖራቸውን በመጠቀም በዓመቱ መጨረሻ ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዳይስፋፋ የሚታገሉትን እውቅና የሚሰጣቸው ሲሆን፥ ሌብነትን የሚያሳልጡትን ደግሞ ተጠያቂ ይደረጋሉ ብለዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር ወዶ አጦ በበኩላቸው የሀገራችን የፀረ-ሙስና ትግል ውጤታማ እንዲሆን አደረጃጀቶችን ማጠናከር ይገባል፡፡ በተቋማት ላይ ያሉ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ጠንክረው መስረት ከቻሉ የምንፈልገውን ለውጥ ማምጣት እንችላለን ብለዋል፡፡




ሁላችንም በጋራ መስራት ከቻልን ሀገሪቱ ወደ ፈለገችበት የእድገት ደረጃ በማሻገር ከሙስናና ብልሹ አሰራር ነፃ ማውጣት እንደምንችል አምናለሁ ብለዋል፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚቻለው የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች ከተቋሙ አመራር ጋር በቅንጅት በመስራት እንጂ በተናጠል ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ገልፀዋል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሰራርን ትኩረት አድርጎ የማይሰራ የተቋም ኃላፊ ካለ የፖለቲካ እና አስተዳደራዊ ተጠያቂነት እንዲሁም በሙስና የተዘፈቀ ከሆነ ደግሞ በሙስና ወንጀል ተጠያቂ ይሆናል ብለዋል፡፡

የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር እሸቴ አስፋው ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መሰራት አለባቸው ብለዋል፡፡

በተቋማት ውስጥ የሚገኙ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት፣ የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍል እና የህግ አገልግሎት እንዲሁም ተቋማዊ ለውጥ በቅንጅት መስራት ከቻሉ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል ይቻላል ብለዋል፡፡



# አንድ ግለሰብ ወድቆ ያገኙትን ከ7 ሺ ብር በላይ ለፖሊስ አስረከቡ

አቶ በሽር አህመዲን የተባሉ ግለሰብ ወድቆ ያገኙትን 7 ሺህ 700 ብር የራሴ ያልሆነና ያልለፋሁበት ገንዘብ ነው በማለት ለአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ማስረከባቸውን የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታውቋል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ የግለሰቡን ተግባር አድንቆ ባለቤቱ ያልተገኘንና ወድቆ የተገኘን ንብረት ለሚመለከተው አካል የማስረከብ ልምድ ሊጠናከር እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፏል።

ግለሰቡ የፈፀሙትን ተግባር ፖሊስ አድንቆ ገንዘቡ የእኔነው የሚል ግለሰብ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በመቅረብ መረከብ እንደሚችል አስታውቋል፡፡

ማህበረሰቡ ወድቆ ያገኘውን እና ባለቤቱ ያልተገኘ ንብረትን በአካባቢው ለሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ የማስረከብ ልምድ ሊያዳብር እንደሚገባ የአዲስ አበባ ፖሊስ መልዕክቱን አስተላልፏል፡፡

# የአዲስ አበባ ፀረ-ሙስና ኮሚቴ ከሕዳር 28 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በሕገ ወጥ የተገኘ 43 ሺህ 436 ነጥብ 44 ካሬ ሜትር መሬት ማገዱን አስታወቀ

የኮሚቴው ሰብሳቢ እና የአዲስ አበባ ከተማ የሰላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ሊድያ ግርማ እንደገለጹት÷ እገዳው በምርመራ ወቅት የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ የተከናወነ ነው፡፡

ከሕብረተሰቡ በነፃ ስልክ መስመር፣ በአካል እና በጥቆማ መቀበያ ሳጥኖች ከደረሱ 401 ጥቆማዎች መካከል 133 ለሕግ ምርመራ ቡድን ተመርቷል ብለዋል፡፡


በአሁኑ ወቅትም 130 የምርመራ መዝገቦች በማደራጀት እንደየ ወንጀሉ ባህሪ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ እና ወንጀል ፈፃሚዎችን በመለየት ላይ እንገኛለን ነው ያሉት፡፡

ከተደራጁ የምርመራ መዝገቦች መካከል 10 የምርመራ መዝገቦች ተጠናቀው ለፌደራል ዐቃቤ ሕግ መቅረባቸውን እና በ56 ግለሰቦች ላይ ክስ መቅረቡን አንስተዋል፡፡

የወንጀል አፈፃፀሙም የመንግስት ባዶ ቦታዎችን፣ ለከተማ ውበት ተብለው የተቀመጡ አረንጓዴ ቦታዎች፣ የመንግስት ቬዶችን ለግለሰቦች ይዞታ ማረጋገጫ መስጠት፣ ሀሰተኛ ካርታ በማዘጋጀት እና ሌሎችም የወንጀል ዘዴዎችን በመጠቀም የተፈፀመ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የወንጀሉ ፈፃሚዎች ከመሬት ይዞታ ባለሙያ እስከ የመንግስት ከፍተኛ አመራሮች መሆናውም በመግለጫው ተጠቅሷል፡፡

እንዲሁም ከተለያዩ ደላሎች ጋር በጥቅም በመመሳጠር የሊዝ ዋጋ 29 ሚሊየን 249 ሺህ 955 ብር የሚገመት ጉዳት ማድረሳቸው በምርመራ መረጋገጡን የኮሚቴው ሰብሳቢ ተናግረዋ።







# ህገ-ወጥ የመሬት ወረራን ስርዓት ለማስያዝ በትኩረት እየተሠራ ነው - አቶ አሻድሊ ሀሰን

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሚስተዋለውን ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ ስርዓት ለማስያዝ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አሻድሊ ሀሰን ገለጹ፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ በክልሉ የሚስተዋለውን ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ መልክ ለማስያዝ ከተቋቋመው ዐቢይ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ጋር እስካሁን የተሠሩ ሥራዎችን ገምግመዋል።

በመድረኩ ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራን ለመከላከል የተለዩ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አቶ አሻድሊ ገልጸዋል።

የክልሉ መንግስት በቀጣይ በሕገ-ወጥ የመሬት ወረራ ላይ በሚሣተፉ አካላት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳልም ነው ያሉት፡፡

የፀረ-ሙስና ኮሚቴው ባለፉት ወራት ያከናወናቸውን ሥራዎች በመገምገም የቀጣይ አቅጣጫ ማስቀመጡንም የክልሉ ኮሙኒኬሽን መረጃ ያመላክታል፡፡

# የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ከ2 ሺህ 700 በላይ አጠራጣሪ የፋይናንስ ማጭበርበር ጥቆማዎች እንደደረሱት አስታወቀ

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ2 ሺህ 700 በላይ አጠራጣሪ የፋይናንስ ማጭበርበር ጥቆማዎች እንደደረሱትና አንድ መቶ ሰባ ሰባቱን ለሕግ አካላት ማስተላለፉን ገለጸ።

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ሙሉቀን አማረ እንደገለጹት አገልግሎቱ የሀገሪቷ የፋይናንስ ደህንነት ለማረጋገጥ ባንኮችና እንሹራንሶችን እንዲሁም ከማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሰራ ነው።

በተለይ በታክስ ማጭበርበር፣ ከህጋዊ የፋይናንስ ተቋማት ውጭ የሚንቀሳቀስ የውጭ ምንዛሪ ዙሪያ ከፍትህ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና ቅንጅት እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህም ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከቀረቡት 2 ሺህ 700 አጠራጣሪ የፋይናንስ ጥቆማዎች ውስጥ 177 የሚሆኑትን አጠራጣሪ ጥቆማዎች በመለየትና በመተንተን ለህግ አካላት ማስተላለፉን ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም በህገ ወጥ መንገድ የተገኘውን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ መጠቀም ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከ166 አገሮች ጋር መረጃ መለዋወጥ ተችሏል ብለዋል።

መድረኩ ተግባር ተኮር የሆነ የፋይናንስ ደህንነትን ማረጋገጥ፣ በዘርፉ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርም ገልጸዋል።

የፌዴራል የፍትህና ህግ ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ዘካርያስ ኤርጉላ በበኩላቸው ተቋሙ የሀገሪቱን የፋይናንስ ደህንነት ለማረጋገጥ በኦፐሬሽንና ወንጀሎችን በጋራ መከላከል ላይ በትብብር እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

በዚህም ሽብርን በገንዘብ መደገፍና በህገ ወጥ የተገኘውን ገንዘብና ሀብት ህጋዊ አስመስሎ መጠቀም ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በጋራ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

መድረኩ የዘመኑን የቴክኖሎጂና ስልቶችን በመጠቀም በፋይናንስ ዙሪያ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በቅንጅት ለመከላከል ያግዛል ያሉት አቶ ዘካርያስ፣ ከፋይናንስ ውጭ በማዕድን፣ በብረታ ብረትና ሌሎች ሀብቶች ላይ ጭምር የሚፈፀሙ የማጭበርበርና የቅሸባ ወንጀሎችን ለመከላከል በጋር እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በመድረኩ ላይ ከተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት፣ ከፍትህና ህግ ማስከበር የተውጣጡ አመራሮችና ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ መሆናቸውን ተዘግቧል።



# ከ749 ሚሊየን ብር በላይ በሀሰተኛ ደረሰኝ የተጭበረበረ ገቢ እንዲከፈል ማድረጉን የአማራ ገቢዎች ቢሮ ገለጸ

ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ749 ሚሊየን 635 ሺህ ብር በላይ በሀሰተኛ ደረሰኝ የተጭበረበረ የመንግስት ገቢ እንዲከፈል ማድረጉን የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ ገለጸ፡፡

በቢሮው የግብር ትምህርት እና ኮሙኒኬሽን የሥራ ሂደት ዳይሬክተር አቶ አግማስ ጫኔ እንደገለጹት÷ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ1 ሺህ 418 ግብር ከፋዮች 2 ሺህ 914 የሀሰተኛ ደረሰኝ ማግኘት ተችሏል፡፡

ቢሮው ባከናወነው የክትትል ስራም 749 ሚሊየን 635 ሺህ 754 ብር ለመንግስት ገቢ ማድረግ መቻሉን አንስተዋል፡፡

የግብር ሥወራና ማጭበርበር ችግርን ለመከላከል መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ሥልቶችን ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

ቢሮው የተጠናከረ የክትትል ቡድን አደራጅቶ እየተከታተለ መሆኑን ጠቅሰው÷ የታክስ ኢንተለጀንስና የኦዲት ምርመራ ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ዳይሬክተሩ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ገልጸዋል፡፡

ከዚህ ባለፈም ችግር የተገኘባቸው ተቋማት ላይ አስተዳደራዊና ሕጋዊ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ነው የገለጹት፡፡

ከሶስተኛ ወገን 539 ጥቆማዎች ለገቢ ተቋሙ ደርሰው 495 ጥቆማዎችን በማጣራት 100 ሚሊየን 791 ሺህ 457 ብር ገቢ ማግኘት መቻሉን አስታውሰዋል፡፡

የስራ ግብር በማይከፍሉ 837 የግል ድርጅቶች ላይ በተደረገ ክትትል 158 ሚሊየን 128 ሺህ 372 ብር የስራ ግብር ገቢ መደረጉንም ገልፀዋል፡፡



# በሲዳማ ክልል በሙስና የተጠረጠሩ ግለሰቦችን የመለየት ስራ እየተከናወነ ነው

የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ደስታ ሌዳሞ የክልሉን ፀረ-ሙስና ኮሚቴ የስራ እንቅስቃሴን ገምግመዋል።

በግምገማው ወቅት ከመቶ በላይ ጥቆማዎች መቅረባቸውን የፀረ-ሙስና ኮሚቴው በሪፖርቱ አመላክቷል።

በቀረቡት ጥቆማዎች መሰረትም በቂ መረጃና ማስረጃ የተገኘባቸው ተጠርጣሪዎች መለየታቸው ነው የተገለጸው።

በቅርቡም ግለሰቦችን ተጠያቂ ማድረግ እንደሚጀመር ኮሚቴው መግለጹን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ ቤት መረጃ ጠቅሶ ፋና ዘግቧል።

አቶ ደስታ ኮሚቴው የሄደበት ርቀት ጥሩ መሆኑን ጠቅሰው÷ በክልሉ ሙስናን ለመግታት ኮሚቴው የጀመረውን ስራ በማጠናከር ምርመራውን አጠናቆ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር አቅጣጫ አስቀምጠዋል።




# ሀሰተኛ ደረሰኝ በማተም እና በማሰራጨት ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸው ተገለፀ

በገቢዎች ሚኒስቴር የአዳማ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በከተማዋ ሀሰተኛ ደረሰኝ በማተም በማሰራጨት በህገ-ወጥ ተግባር ላይ ተሰማርተው ሲያጭበረብሩ የነበሩ ግለሰቦችን በተደረገ ክትትል በቁጥጥር ስር ማዋል መቻሉን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ሰለሞን ደርቤ ገልጸዋል፡፡

ግለሰቦቹ በከተማዋ ህጋዊ ፈቃድ አውጥተው በተሰማሩ ድርጅቶች እና ሆቴሎች የንግድ ስም በመጠቀም ግብይት ባልተፈፀመበት ግብይት እንደተፈፀመ አስመስለው ሀሰተኛ ደረሰኝ በማተም እና በመሸጥ ላይ የተሰማሩ መሆናቸውን አቶ ሰለሞን አክለው ገልጸዋል፡፡

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለሁለት ወራት ያክል በተደረገ ክትትል በተለያዩ 35 በሚሆኑ ህጋዊ ድርጅቶች ስም የታተመ ሀሰተኛ ደረሰኝ የተያዘ ሲሆን ዋነኛ የድርጊቱ ተጠርጣሪዎችን እጅ ከፈንጅ በቁጥጥር ስር ማዋል ተችሏል፡፡

እንደ ስራ አስኪያጁ ገለፃ እነዚህ ኃላፊነት የጎደላቸው ህገ-ወጥ ግለሰቦች መሰብሰብ ያለበትን ግብር በመሰወርና ሀገር ልታገኝ የነበረውን ገቢ ከማሳጣት ባለፈ ኢኮኖሚው ላይ ቀውስ በመፍጠር በሀገር ላይ ከፍተኛ




ኪሳራ ሲያደርሱ መቆየታቸውንም አብራርተዋል፡፡

በተለይም ግለሰቦቹ በቁጥጥር ስር ሲውሉ ከሀሰተኛ የወጪ እና የገቢ ደረሰኝ ህትመት እና ስርጭት ባለፈ ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች፣ የነዋሪነት መታወቂያና ሌሎች ሀሰተኛ ሰነዶችንም ጭምር በማዘጋጀት ከገቢው



ባሻገር ዘርፈ ብዙ ለደህንነት ስጋት የሚሆኑ ወንጀሎችን ሲሰሩ መቆየታቸው ተደርሶበታል፡፡

ህጋዊ የንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩ ያሉ ግለሰቦች ወይም የድርጊቱ ሰለባዎች በበኩላቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ባደረገው ክትትል ህገ-ወጥ ግለሰቦቹን በቁጥጥር ስር




ማዋሉ በድርጅታቸው ላይ ሊደርስ የነበረውን ተጨማሪ ኪሳራ ማስቀረት መቻሉን አንስተዋል፡፡ በመሆኑም ድርጊቱ ወንጀል እና የሀገር ክህደት ጭምር በመሆኑ አስተማሪ ቅጣት ሊሰጣቸው እንደሚገባም ማሳሰባቸውን ገቢዎች ሚኒስቴር በፌስቡክ ገፁ አስፍሯል።


# ሀገሪቱ ከ672 ሺ የአሜሪካን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ እንድታጣ ያደረገው ተከሳሽ በጽኑ እስራት እና በገንዘብ ተቀጣ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ የተደራጁና ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል ዐቃቤ ሕግ ከብሔራዊ ባንክ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ሀገራችን ከ672 ሺ የአሜሪካን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ እንድታጣ አድርገሃል ባለው ግለሰብ ላይ ክስ መስርቶበት በ6 ዓመት ከ6 ወር ፅኑ እስራት እና በ30 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ እንዲሁም የተከሳሽ ህዝባዊ መብቶቹ ለ2 ዓመት እንዲታገዱ ሲል ወስኖበታል፡፡

ዐቃቤ ሕግ ከድር ሽሞሎ አሊ በተባለው ተከሳሽ ላይ ክስ ሊመሰርት የቻለው በ2000 ዓ.ም የወጣውን የባንክ ስራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 3/1/ እና 58/1/ ስር የተደነገገውን ተላልፏል በሚል ነበር፡፡

የዐቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያስረዳው ተከሳሽ የባንክ ስራን ለመስራት ከብሔራዊ ባንክ የተሰጠ ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው ካልተያዙት ግብረ-አበሮቹ ጋር በመሆን ከቀን 03/05/2004 ዓ.ም እስከ ቀን 01/07/2008 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያት በሳዑዲ አረቢያ እና ዱባይ ሀገር የሚገኙ ግለሰቦች ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ሲፈልጉ እዚያው ሀገር የሚገኙት ያልተያዙ ግብረ-አበሮቹ ገንዘቡን ተቀብለው በስልክ መልዕክት የሚላክላቸውን ሰዎች ስም፣ አድራሻ እና የገንዘቡን መጠን በሚያስተላልፉለት መሰረት ገንዘቡን ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ አምስት ግለሰቦች እና እንዲሁም ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀረበው ኦዲት ሪፖርት ውስጥ ለተጠቀሱት ግለሰቦች ለ1,643 ጊዜ በሐዋላ መልዕክት በጠቅላላው ብር 13 ሚሊዮን 182 ሺ 200 ብር የተለያዩ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎችን በመጠቀም ወደ ተለያዩ የሐገሪቱ ክፍሎች በመላኩ፥ ይኸውም በህጋዊ ገንዘብ አስተላላፊዎች አማካኝነት ገንዘቡ ቢላክ ኖሮ ሐገሪቱ ልታገኝ የነበረውን 672 ሺ 701 የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሬ እንድታጣ ያደረገ በመሆኑ ያለፈቃድ የባንክ ስራ መስራት ወንጀል ዐቃቤ ህግ ክስ መስርቶበታል፡፡

ተከሳሹ የተከሰሰበት ክስ በችሎት ተነቦለት የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም፣ ጥፋተኛም አይደለሁም ብሎ



ክዶ ተከራክሯል። ዐቃቤ ህግም ተከሳሹ ክዶ የተከራከረ በመሆኑ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል። ፍርድ ቤቱም የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮ ተከሳሹ በቀረበበት ክስ ስር እንዲከላከል ብይን ከሰጠ በኋላ ተከሳሽ ያልቀረበ በመሆኑ በሌለበት ፍርድ በመስጠት ተከሳሹ ይከላከል በተባለበት ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ነህ ብሎታል፡፡

በስተመጨረሻም ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 14ኛ ወንጀል ችሎትም ተከሳሽን ያርማል ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ያስተምራል በሚል በ6 ዓመት ከ6 ወር ፅኑ እስራት እና በ30 ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ እንዲሁም የተከሳሽ ህዝባዊ መብቶቹ ለ2 ዓመት እንዲታገዱ ሲል ወስኖበታል፡፡



# ከመርከብ ግዢ ጋር በተያያዘ የተከሰሱት የቀድሞ የ"ሜቴክ" የሕግ ክፍል ኃላፊ በእስራት እና በገንዘብ ተቀጡ

ከመርከብ ግዢ ጋር በተያያዘ የተከሰሱት የቀድሞ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪግ ኮርፖሬሽን የሕግ ክፍል ኃላፊ በ6 ዓመት ከ6 ወራት ጽኑ እስራትና በገንዘብ እንዲቀጡ ተወሰነ።

የቅጣት ውሳኔው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ተወስኗል።

የቅጣት ውሳኔ የተወሰነባቸው ተከሳሽ በወቅቱ ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ቀርተው በሌሉበት ጉዳያቸው ሲታይላቸው ቆይተው ከሁለት ዓመት በኋላ ፍርድ ቤት የቀረቡት የቀድሞ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪግ ኮርፖሬሽን የሕግ ክፍል ኃላፊ የነበሩት ኮሎኔል መሐመድ ብርሃን ናቸው።

ዐቃቤ ሕግ በጥር 6 ቀን 2011 ዓ/ም የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት አባይ እና አብዮት ከተባሉ ሁለት መርከቦች ግዢ ጋር በተያያዘ ከ544 ሚሊዮን ብር በላይ ጉዳት ደርሷል በሚል ሜጀር ጀኔራል ክንፈ ዳኘውን ጨምሮ ከ10 በላይ ተከሳሾች ላይ የሙስና ወንጀል ክስ መመስረቱ ይታወሳል።

ክሱ ከቀረበ በኋላ ኮሎኔል አዜብ ታደሰ ሀይሉ፣ ሻምበል ይኩኑ አምላክ ተስፋዬ፣ ሻምበል ሰመረ ኃይሌ ሐጎስ እና አቶ ሰሎሞን ኃይለሚካኤል ክሱ ተቋርጦላቸዋል፡፡

በክሱ ተካተው የነበሩ ኮሎኔል ሙሉ ወልደገብርኤል፣ ብርጋዴር ጄኔራል ጠና ቁሩንዲ እና ኮሎኔል ተከስተ ኃይለማርያም ደግሞ በፍርድ ቤቱ ተላልፎባቸው የነበረውን ፍርዳቸውን ጨርሰው ከእስር ተፈተዋል።

በ7ኛ ተራ ቁጥር በተከሳሽነት የተቆጠሩት በመርከብ ግዢ ኮሚቴ ነበሩ ተብለው በክሱ ተካተው የነበሩት እና በወቅቱ ባለመቅረባቸው ምክንያት በሌሉበት ጉዳያቸው ሲታይ ቆይቶ ከሁለት ዓመት በኋላ ፍርድ ቤት ቀርበው ክርክር ያደረጉት ኮሎኔል መሐመድ ብርሃን በሚመለከት ዓቃቤ ሕግ የቀረበባቸውን የሰው ምስክር እንዲከላከሉ ብይን ተሰጥቶ ቆይቷል።

በብይኑ መሰረት በተለያዩ ቀናቶች የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን በተገቢው ማስተባበል አልቻሉም ሲል በአንቀጽ 411/ንዑስ ቁጥር 2 መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ ተላልፎባቸዋል።

ተከሳሹ ኮሎኔል መሐመድ ብርሃን በሠላም ማስከበር ዘርፍ ለሀገር ያበረከቱትን አስተዋፅኦ እና ሀገራዊ ልማት ላይ ያደረጉትን ተሳትፎ ጨምሮ ሰባት ቅጣት ማቅለያ አስተያየት በጽሑፍ አቅርበው ተይዞላቸዋል።

ዐቃቤ ሕግ ድርጊቱ በስምምነት የተፈጸመ መሆኑን ጠቅሶ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እንዲጣልለት ያቀረበው የቅጣት ማክበጃ አስተያየት የተያዘለት ሲሆን፥ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ፍርድ ቤቱ በ6 ዓመት ከ6 ወራት ጽኑ እስራትና በ10 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል።

በዚሁ መዝገብ ክስ ቀርቦባቸው የነበሩት የቀድሞ የሜቴክ ዋና ዳይሬክተር ሜጀር ጀነራል ክንፈ ዳኘውን በሚመለከት ግን በቀረበባቸው ክስ ላይ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን በማሰማት ሂደት መሆናቸው ተመላክቷል።

# “ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከልና መልካም ሥነ-ምግባርን ማስፈን” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሥልጠና ለፍርድ ቤቱ የአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞች ተሰጠ

በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍል “ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከልና መልካም ሥነ-ምግባርን ማስፈን” በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሥልጠና ከፍርድ ቤቱ የአስተዳደር ዘርፍ ለተውጣጡ 120 ሠራተኞች በፍርድ ቤቱ የስብሰባ አዳራሽ መሰጠቱ ተገለፀ፡፡





ሥልጠናው በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ ሙስናን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ትኩረት አድርጎ የተሰጠ ሲሆን፤ ዓላማው የሥልጠናው ተሳታፊዎች በፍትህ ስርዓት ውስጥ ሙስናን መከላከል ያለውን አስፈላጊነት እንዲረዱ ለማድረግ እንዲሁም በተቋሙ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች ውስጥ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን እንዲለዩና ለሙስና መከሰት ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎችን ለመቀየር የሚያስችል የመፍትሄ ሃሳብ ማመንጨት እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡

በፍትህ ስርዓት ውስጥ ተገልጋዮች መረጃ ለማግኘት በውስብስብ፣ በአሰልቺና በተንዛዛ ቢሮክራሲ እንዲያልፉ መደረጉ፣ ባለሙያዎች በሙያ ሥነ-ምግባራቸው የጎለበቱ ካልሆኑና በሙያቸውም ብቁ ሆነው ካልተገኙ ለሙስና የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ መሆኑ፣ የተጠያቂነትና የግልጽነት አሰራር የላላ መሆኑ፣ የገቢ ማነስ (የደመወዝ ማነስ)፣ የወዳጅነትና የማኅበራዊ ግንኙነት ተጽእኖ መኖር፣ ሙስናን እንደነውር ያለማየት ልማድ፣ በሙሰኞች ላይ የሚወሰድ እርምጃ የላላ መሆን፣ በሙያተኞች መካከል የሚፈጠር መሻረክ (Collusion) እና ሌሎችም በፍትሕ ሥርዓቱ ውስጥ የሙስና መከሰቻ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጠቅሷል፡፡

በፍትህ ሥርዓት ውስጥ ሙስና ወይም ብልሹ አሰራር ሊኖር እንደሚችል የሚጠቁሙ ሁኔታዎችና የሙስና መከሰቻ ሁኔታዎች፣ በፍትህ ሥርዓት ውስጥ የሙስና አዝማሚያ ጠቋሚዎች፣ በፍርድ ቤቶች አካባቢ ያሉ የሙስና መከሰቻ አጋጣሚዎችም በሥልጠናው ተዳስሰዋል፡፡

በፍትህ ሥርዓት ውስጥ የሚፈጸም ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች በሥልጠናው ላይ ማብራሪያ የተሰጠበት ሲሆን፣ ከጉዳቶቹ መካከል የህግ የበላይነትን አደጋ ላይ እንዲወድቅ ማድረጉ፣ ወንጀሎች እንዲበራከቱ ምክንያት መሆኑ፣ በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ያሉ መልካም እሴቶች እንዲሸረሸር ማድረጉ፣ ለሀገር ልማትና ኢኮኖሚ እድገት እንቅፋት መሆኑ፣ ሰብአዊ መብቶች አደጋ ላይ እንዲወድቁ ማድረጉ፣ ዜጎች ከተቋማት የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዳያገኙ ማድረጉ፣ ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዳይፈቱ ምክንያት መሆኑ፣ በህገመንግስቱ ተፈጻሚነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ እና ሌሎችም አሉታዊ ውጤቶች ተብራርተዋል፡፡

በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና ድርጊቶችን ለመከላከል የሚረዱ የሙስና መከላከያ ስልቶችም በሥልጠናው ላይ ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

ሥልጠናው ያተኮረው በሙያ ትውውቅ፣ በፌደራል ፍርድ ቤቶች የአስተዳደር ዘርፍ ሠራተኞች መመሪያዎች እና ደንቦች፣ በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እንዲሁም በመንግሥት ሠራተኞች የዲሲፕሊን አፈጻጸም መመሪያ እና የሥነምግባር መርሆዎች ላይ ነው፡፡

ሥልጠናውን የተሰጠው በፍ/ቤቱ የሕግ ጥናትና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በአቶ አሮን ደኀል፣ በሰው ሐብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በአቶ ያሬድ ለገሰ እንዲሁም በዳይሬክቶሬቱ ከፍተኛ ባለሙያ በአቶ ምሕረት አይቸው እና በሴቶችና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት ቡድን መሪ በሆኑት በአቶ አሌክሳንደር አዳም ሲሆን፥ የሥልጠናው ተሳታፊዎች በፍርድ ቤቱ የሚኖራቸውን መብቶች እንዲሁም ከእነርሱ የሚጠበቁ ግዴታዎች በተመለከተ ከተሰጣቸው ሥልጠና ግንዛቤ ሊጨብጡ እንደቻሉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌስቡክ ገፁ አጋርቷል፡፡

# 9 ሚሊየን ብር የሚያወጣ ተሽከርካሪን ይዞ የተሰወረው ሹፌር በጽኑ እስራትና በገንዘብ ተቀጣ

የትግራይ ክልል ንብረት የሆነን 9 ሚሊየን ብር የሚያወጣ "ላንድ ክሮዘር ፕራዶ" ተሽከርካሪን ይዞ የተሰወረው ሹፌር በጽኑ እስራትና በገንዘብ ተቀጣ።

የቅጣት ውሳኔው የተወሰነው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው።

የቅጣት ውሳኔ የተወሰነበት ተከሳሽ አሸናፊ ረዳኢ የሚባል ሲሆን፥ በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ተከራይቶ ይኖር እንደነበር ጠቅሷል።

ተከሳሹ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳደር ጽኅፈት ቤት ከመስከረም 5 ቀን 2013 ዓ.ም እስከ መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በሹፌርነት ተቀጥሮ ሲሰራ እንደነበር በክሱ ተገልጿል።

በዚህ ጊዜ ለሥራ ወደ አዲስ አበባ ለሚመጡ የሥራ ኃላፊዎች የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥበት ተረክቦ የነበረውን ንብረትነቱ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሆነ የታርጋ ቁጥር ኮድ 4-01423 (ትግ) እንዲሁም የፕሮቶኮል ታርጋ ቁጥር ኮድ 2-76686 የሆነ ዘጠኝ ሚሊየን ብር የሚገመት ነጭ "ላንድ ክሮዘር ፕራዶ" ተሽከርካሪ በእጁ ይዞ መቆየቱ በክሱ ተመላክቷል።

ከሚያዝያ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ከነመኪናው በትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር የሽግግር መንግስት አስተዳደር ጽኅፈት ቤት ተዘዋውሮ እንዲሰራ የተመደበ ቢሆንም መኪናውን ይዞ የተሰወረና መኪናውን ያጠፋው መሆኑን ጠቅሶ ዐቃቢ ህግ በከባድ የእምነት ማጉደል ሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦበታል።

ተከሳሹ በየካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የቀረበበትን ክስ ከደረሰውና በንባብ ከተሰማ በኋላ ወንጀሉን አልፈጸምኩም ሲል የዕምነት ክኅደት ቃሉን ሰጥቷል።

ዓቃቤ ሕግ በበኩሉ ፥ ለወንጀሉ መፈጸም የሚያስረዱልኝ አምስት ምስክሮች ስላሉኝ ይሰማልኝ ሲል ጠይቋል።

ፍርድ ቤቱም በተለያዩ ቀናቶች የዐቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል ካዳመጠ በኋላ ተከሳሹ የቀረበበትን የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቷል።

ተከሳሹ የመከላከያ ማስረጃዎችን ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ማስረጃን በተገቢ መንገድ ማስተባበል አልቻለም በማለት በተከሰሰበት የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ንዑስ ቁጥር 2 መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ አስተላልፎበት ነበር።

ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ያቀረበውን የቅጣት ማቅለያ አስተያየቶችን እና ዐቃቤ ሕግ ቅጣቱ ከፍ ብሎ እንዲጣልለት ያቀረበው የቅጣት ማክበጃ አስተያየት በመያዝ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ንዑስ ቁጥር 2 መሰረት ተከሳሹን በ6 ዓመት ከ6 ወራት ጽኑ እስራትና በ10 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ መወሰኑን ፋና ዘግቧል።

ብሔራዊ የሙስና ድርጊቶች ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች
ስልክ: 9555
አጭር የፅሁፍ መልዕክት: 9555
ድረ ገፅ: http://www.9555pmo.et/
ኢሜይል: http://9555pmo.et/
ቴሌግራም:https://t.me/PMOfeedback

የሙስናና ብልሹ አሰራር ድርጊቶችን በጥቆማ መስጫ አድራሻዎች ያጋልጡ፣ይጠቁሙ!!

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

ስልክ 011552-77-79
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**www.feaccdars.gov.et**


## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ስልክ 011552-77-92/ 011553-38-52
ሞባይል 0935947533
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ኢ-ሜይል CorruptionReportEthiopia@feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

# ርዕሰ -አንቀፅ

## የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተልዕኮ ማሳካት ሚናቸውን በብቃት መወጣት አለባቸው!!

ኮሚሽኑ ተልዕኮውን በብቃት ለማሳካት የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በመንግስት ተቋማት፣ የልማት ድርጅቶች እና ህዝባዊ ተቋማት እንዲደራጁ አድርጓል:: አደረጃጀት ከመፈጠር በተጨማሪ በአብዛኛው በሥነምግባራቸው የተሻሉ የተባሉት ሰዎች በተቋማት አደረጃጀቱ ውስጥ ተካተው የፀረ-ሙስና ትግሉን እንዲመሩና እንዲያስተባብሩ ሁኔታዎች አመቻችቷል::

የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች ዋና ተልዕኳቸው የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርቶችና ሥልጠናዎችን በማስፋፋት የሥራና የሙያ ሥነምግባርን የተላበሰ፣ በህዝብ አገልጋይነት ስሜት የሚንቀሳቀስ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል አመራርና ሠራተኛ እንዲፈጠር ማድረግ፤ በተቋም ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ተጋላጭ የሆኑ አሠራሮች ላይ የአሠራር ሥርዓት ጥናት በማካሄድ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማስተግበር እና የተቋሙን ሁሉንም አመራርና ሠራተኞች ሀብትና ንብረት እንዲያስመዘግቡና እንዲያሳድሱ በማድረግ የግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፋን፣ የሙስና ወንጀል እንዲጋለጥ፣ እንዲመረመር እና በአጥፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ መከታተል፥ የተመዘበረ ሀብት እንዲመለስ በማድረግ የተቋሙን የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ስራ ማስተባበር ነው::

ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት በትክክል ከማከናወን አንፃር ሥራቸውን በትጋት የሚያከናወኑ እንዳሉ ሁሉ ሥራቸውን በተገቢ ሁኔታ የማያከናወኑ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች መኖራቸው የሚደበቅ ጉዳይ አይደለም:: በሌለ በኩል በተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተልዕኳቸውን በትክክል እንዲወጡ ተገቢውን ክትትልና ግምገማ የሚያደርጉ የተቋም የበላይ ኃላፊዎች እንዳሉ ሁሉ ደግሞ የስነምግባር መከታተያ ክፍል በተቋም ውስጥ ስለመኖራቸው የማያወቁና ትኩረት የማይሰጡ፣ ክትትልና ግምገማ የማያደርጉ የበላይ አመራሮችም በርካታ ናቸው::

እንዲሁም በተቋማት ውስጥ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን በመስጠት ለፀረ-ሙስና ትግል ተባባሪና አጋር የሚሆኑ የተቋም የውስጥና የውጪ ተገልጋዮችን በትክክል የማነሳሳትና የመጠቀም ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሠራር በመጠኑም ቢሆን እየቀነሰ ሲገኝ፥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ለጠቋሚዎች ምቹ ሁኔታ በትክክል በማይፈጥሩና በማያነሳሱ፥ ለሥራው ትኩረት ሰጥተው በማይንቀሳቀሱት ተቋማት ውስጥ ደግሞ የሙስና እና ብልሹ አሠራር እየተበረከተ ይገኛል::

በሌለ በኩል በተቋም ውስጥ በክትትልና ቁጥጥር ላይ ያተኮሩ ሥራዎች የሚያከናወኑ የሥራ ክፍሎች ጋር በተለይ የኦዲት፣ የህግ አገልግሎትና የተቋማዊ ለውጥ ሥራ አመራር ቅንጅት በመፍጠር የፀረ-ሙስና ትግሉን በትኩረት ለማካሄድ የሚቀንቀሳቀሱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ብዙ አለመሆናቸውን የጥናት ሰነዶች ስለሚያመለክቱ፥ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ይህን ቅንጅታዊ አሰራር የሥራ አካል በማድረግ ለመንቀሳቀስ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል::

በተጨማሪም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋማት አሠራርና አደረጃጀት ላይ በቂ ግንዛቤ በመያዝና የራስን የሙስና መከላከል ክህሎትን በማሳደግ፥ የተልዕኮ መወጣት ሥራዎችን ከተቋማት የበላይ አመራሮች ጋር በመቀራረብና በማማከር ትግል ማድረግ አለባቸው:: ከዚህም ባለፈ የተቋማት የውስጥና የውጪ ተገልጋዮች የጸረ-ሙስና የትግል አጋርና ተባባሪ እንዲሆን በትጋት በማከናወን የተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራር የመከላከል ሥራ በትኩረትና በጥንቃቄ እንዲከናወን እንዲሁም ተቋማት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር የመከላከል የሥራ ባህሪ ያለቸውን ተግባራት ከሚያከናወኑ የሥራ ክፍሎች ጋር ቅንጅታዊ እቅድ በማቀድ እንዲከናወን እና የሙስና መረጃ ጥቆማዎች ላይ የሚገጥሙ ጋሬጣዎችን ለኮሚሽኑ በሪፖርት በወቅቱ ማሳወቅ እንዳለበት አቅጣጫ በማስቀመጥ ሁሉም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራዎችን በቁርጠኝነትና በሀገራዊ ስሜት በትጋት ማከናወን ይኖርባቸዋል::

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በቀጣይ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ተልእኮን በትጋትና በቅልጥፍና ለማሳካት ሚናቸውን በትክክል እንዲወጡ የሥነምግባር ግንባታና የሙስና መከላከል ሥራ ዕውቀትና ክህሎት ማሳደጊያ ሥልጠና የመስጠት፣ በየጊዜ የልምድ ልውውጥ መድረኮችን የማመቻቸት እንዲሁም በየተቋማቱ የሚገኙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በአካል ጉብኝት የሱፐርቭዥን ሥራዎችን በመሥራት የድጋፍና ዕገዛ ሥራዎችን የማድረግ ሥራዎችን አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል::

# ቆይታ



**የፌደራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በህግ የተሰጣቸውን ሙስናን የመከላከል ተልዕኮ በአግባቡ ለመወጣት የትውልድን የሥነምግባር እና የሞራል እሴቶች የመገንባት፣ በመንግስት ተቋማትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲለዩና እንዲፈቱ የማድረግ፣ ሀብት መመዝገብና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ማድረግና የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና መላውን ህብረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤት እንዲሆን ማስቻል ነው። የስነምግባር የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዲሞክራሲ ተቋማት መካከል አንዱ ነው። ኮሚሽኑን የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመከታተል፣ የመደገፍና የተለያዩ ትብብሮችን የማድረግ ኃላፊነትና ተሰጥቶታል።**

## የተከበሩ አቶ እውነቴ አለነ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ መንግስት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖችን አሰራር የማሻሻል ስራዎችን አጠናክሮ ይቀጥላል

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ የአስረኛ ዕትም እንግዳችን የኢትዮጵያዊ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ክቡር እውነቴ አለነ ናቸው:: የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ ከክቡር እውነቴ አለነ ጋር ያደረገችውን ቆይታ ይዛ ቀርባለች:: መልካም የንባብ ጊዜ...

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡- በመንግስት የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ለፀረ-ሙስና ትግሉ የሚኖረው ፋይዳ ምን ይሆናል ብለው ያስባሉ?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- ሙስና ከሙስና ወንጀልነት አለፍ ብሎ ብሄራዊ የደህንነት ስጋት ወደ መሆን በመድርሱ አጠቃላይ የሰላማችን እና የልማታችን ከፍተኛ አደጋ በሚሆንበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ምክኒያት በአንድ ተቋም ብቻ መከላከል እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ እንደማይቻል መንግስት በመረዳት በርከት ያሉ ባለድርሻ አካለት የሚሳተፉበት የብሄራዊ ፀረ-ሙስና አስተባባሪ ኮሚቴ ተቋቁሟል፤ የፀረ-ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ የተለያዩ አካላት በጋራ መረጃን በማሰባሰብና በመለዋወጥ ሙሰኞች ሲፈጥሩት የነበረውን ማስረጃ የማጥፋት ችግር ለመፍታት ያግዛል:: በሌላ በኩል ደግሞ ሙስና ብሄራዊ የደህንነት ስጋት ደረጃ የደረሰበት ሁኔታ ስለሆነ ከፍተኛ ትኩረት በመንግስት ተሰጥቶት እየተሰራ መሆኑን ህብረተሰቡ በማሳወቅ ተሳትፎ እና አስተዋፆኦ እንዲያደርግ የሚያበረታታ ነው:: የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ በጥሩ ጎኑ የማየው ሲሆን፤ ነገር ግን እንዲህ አይነት ኮሚቴ ጊዜያዊ ኮሚቴ እንጂ ዘላቂነት ያለው ኮሚቴ ባለመሆኑ ምክኒያት የተቋም ጥንካሬን አይፈጥርም:: ስለሆነም ሙስናን በመታገል ማስረጃ በማሰባሰብ፣ በመመርመርና በመክሰስ ሚና ያላቸው አካላት ተቋማዊ በሆነ መንገድ እንዲጠናከሩ ማረግ ይገባል:: በእኔ በኩል አሁን የተጀመረው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ እንደ አንድ የመሸጋገሪያ ኃይል ሁኖ የሚያግዝና ችግሩን በተወሰነ ደረጃ የሚያቃልል፣ ህብረተሰቡም አሜኔታ የሚያሳድርበት ሁኔታ መፈጠሩ ጥረ ነገሩ ሲሆን፤ በዘላቂነት ተቋማዊ ግንባታ የማጠናከር ስራ ካልተከናወነ ችግሩን መፍታት እንደማይቻል በመረዳት ተቋማዊ ወደ ሆነ የፀረ-ሙስና ትግል መግባት ያለብን ይመስለኛል::

በተለይ በክልል ደረጃ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለህዝብ እረሮ ምንጭ የሆኑ፣ የመልካም አስተዳደር ችግር በመሆን ተገልጋይን በየጊዜው እያማረሩ ያሉበት ዘርፎች የተለየበት ሁኔታ ሲሆን፤ በዋናነት በገጠርና በከተማ መሬት ጋር ተያይዞ ህዝቡ ከፍተኛ የሆነ ምሬት ውስጥ ገብቷል::

ስለዚህ የክልሉ መንግስት አንዱ ትኩረት ያደረገው ከኢንቨስተመት ጋር ተያይዞ የከተማና የገጠር መሬት ላይ ነው፤ እንዲሁም የማዕድን ፍቃድ አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ፍቃድ ለመውሰድ ሲባል በየቦታው የሚመጡ ሀሰተኛ ሰነዶች ስላሉ በልዩ ሁኔታ ትኩረት ተሰጦ እየተሰራ ነው:: ፍትህ አካባቢ/አደባባይ ላይ የሚሰጡ አስተማሪ ያልሆኑ ቅጣቶች ሲታይ ሙሰኞች/ሌቦች በቅሌታቸው ልክ አስተማሪ ቅጣት እየተሰጠ አይደለም፤ ይህ ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን፣ ሲስተሙ በብልሹ አሰራርና በሙስና የተተበተበ መሆኑን ከህብረተሰቡ የሚመጡ ጥቆማዎች ስላሉ የችገሩ አካባቢዎች ተለይተው እየተሰራ ይገኛል::

በተጨማሪም የክልሉ መንግስት የስራ እድል ፈጠራ ጋር ተያይዞ ከንግዱ ዘርፍና ከንግዱ ማህበረሰብ አካባቢ ያሉ ዋና ዋና ችግሮች ተለይተው በቁርጠኝነት ተግባራዊ ምላሽ በሚያሰጥ መልኩ ለመስራት ቅድመ ዝግጅቶችን በማጠናቀቅ ወደስራ ውስጥ ተገብቷል::

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡- ኮሚሽኑ የዲሞክራሲ ተቋም እንደመሆኑ መጠን የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ያለው ቁርጠኝነት ምን ይመስላል?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ሚና ያለው ተቋም ነው:: ህብረተሰቡን በማስተማር፣ በማንቃት እና ትውልድ በመገንባት እንዲሁም ሙስና ከመፈፀሙ በፊት በርከት ያለ የመከላከል ተግባር መስራት የሚችል ኮሚሽን ነው::

ኮሚሽኑ አንዳንድ ችግሮች ከተፈቱለት ውጤት ማምጣት የሚችልና የጀመራቸውን በርካታ የሚያበረታቱ ነገሮች መኖሩ እረዳለሁ፤ ተቋሙ የዲሞክራሲ ተቋም እንደመሆኑ የመልካም አስተዳደርና የዲሞክራሲ እጦት ችግር በአንድም በሌላ መንግድ ከሙስና መስፋፋት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ዲሞክራሲያችን እንዲያብብ እና መልካም ስነ-ምግባራችን እንዲበለፅግ ሙስናን በመከላከልና በመዋጋት አሁን ካለበት አስከፊ ሁኔታ ዝቅ ማድረግና ማውረድ እንዲሁም በተቻለ መጠን ለዲሞክራሲያችንና ለልማታችን እንቅፋት የማይሆንበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል::

ስለሆነም የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሚደረገውን የሙስና ትግል በከፍተኛ ትኩረት በመከታተልና በተለያዩ መድረኮች አብሮ እያካሄደ ነው:: በቀጣይ ተቋማዊ የሆነ የፀረ-ሙስና ትግል እንዲጠናከርና ሙስናን በተቋም ደረጃ መታገል እንድንችል ከሌሎቹ ተቋማት ይልቅ ትኩረት ሰጠን መስራት እንዳለብን እናምናለን፤ አሁን የተጀመረው ስራ ይሄን የሚያመለካት ነው፤ የሙስና ትግል ቋሚ ኮሚቴው እንደ ቁልፍና የመጀመሪያ አጀንዳ አድርጎ የሚመለከተው ጉዳይ ነው:: ሙስናን ካልተከላከልን ዲሞክራሲያችንና መልካም አስተዳደራችን አደጋ ውስጥ የሚወድቅ በመሆኑ ቅድሚያ የሚሰጠው አጀንዳ ነው::

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡- የስነ-ምግባር ግንባታና ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከመንግስት፣ ከሚዲያ፣ ከኃይማኖት ተቋማት እና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ምን ይጠበቃል ብለው ያስባሉ?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- ሙስና ዘርፈ ብዙ ጉዳት የሚያመጣ ብቻ ሳይሆን በከፍተኛ ሚስጢር እና በከፍተኛ ስልጣን ያላቸው ሰዎች ተቀናጅተው የሚፈፅሙት ወንጀል በመሆኑ ከሌሎች ወንጀሎች በተለዬ ከባድ ወንጀል ነው፤ እንደ ሌሎች ወንጀሎች ተራ የግድያና የስርቆት ወንጀል አይደለም::

ሙስና ታስቦበት ስልጣንን መከታ በማድረግና ከዚህ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም የሚፈፀም ወንጀል በመሆኑ ምክኒያት በአንድ ተቋም ብቻ መከላከልል አይቻልም:: ስለሆነም በተለይ ሚዲያ ስነ-ምግባርን የመገንባትና ሙስናን የመታገል ከፍተኛ ሚና አለው፤ ሙስናን በማጋለጥ፣ ሙስና የሰሩ ሰዎች እጃቸውን እንዲሰበስቡ ለህብረተሰቡ አይን ሆኖ በማገልገል፣ ከዚህም አለፍ ብሎ የምርመራ ጋዜጠኝነትን በመፈፀም ለምርመራ የሚያግዝ ነገር የሚጠቁም እንዲሁም ህብረተሰቡን ማነሳሻ መድረክ ሆኖ ያገለግላል:: ስለሆነም ሚዲያ የማይተካ ሚና በመኖሩ ሌቦችን የማጋለጥ፣ ለትግሉ ተዋናዮች መረጃ የመስጠት፣ ሙስና የሚፈፅሙ ሰዎችን እረፉ ብሎ እንዲገስጣቸው የሚያግዝ መሳሪያ ነው:: ነገር ግን ሚዲያ እስካሁን የሚገባውን ያህል ሚና ተወጥቷል ማለት አይቻልም፤ በአንድም በሌላ መንገድ በዜናዎቻና በዘገባዎች ላይ የተመሰረተ ነው እንጂ ጠበቅ ብሎ የምርመራ ጋዜጠኝነትን በመጀመርና በማጋለጥ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ቆይቷል:: ወደ ስራ የማይገባበት ብዙ ምክኒያቶች አሉት፤ ሙስና የሚፈፅሙ ሰዎች ስልጣንና



ከፍተኛ ትስስር ያላቸው በመሆኑ በተለያየ መንገድ በገንዘብና በስልጣን ሁሉን ነገር ማዳፈን የሚችሉ ናቸው:: በዚህ ረገድ መንግስት ቁርጠኛ ሁኖ ሚዲያው ሙሰኞችን በሚያጋልጡበት ወቅት ችግር እንዳይደርስባቸው ከለላ በመስጠት ሙሰኞች በቁጥጥር ስር መዋሉ አይቀርም:: አንዳንዴ ሙስና የሚፈፅሙ ሌቦችና በስርቆት የበለፀጉ ሰዎች ሚዲያን በመጠቀም ከሙስና ነፃ የሆኑ ሰዎችን ሲሳደቡ፣ ሲዝቱ እና አጀንዳውን ቀምተው ሲያላግጡ እናያለን:: ችግሩ ከራሳቸው የመጣ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ሚዲያ አንዱ የሚቋቋምበት ምክኒያት ስነ-ምግባርን የመገንባትና ሙስናን የመታገል ሚና አላቸው::

ሚዲያ የህብረተሰቡ መብቶችና ጥቅሞች አደጋ ላይ እንዳይወድቁ የመከላከል፣ መረጃ የመስጠትና ድምፅ ሆኖ የማገልገል ሚናውን በራሱ መጫዎት ያለበት ቢሆንም ከፍተኛ የሆነ ጥበቃ ይስፈልገዋል:: ሙሰኞች ተደራጅተው ሲያጠቁት ወይም ደግሞ ጋዜጠኛውን ሲያዋክቡት እረፉ የሚል ስርዓት ያስፈልጋል::

የኃይማኖት ተቋማት ስነ-ምግባር የመገንባት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል:: ሙስና ማለት የስነ-ምግባር ዝቅጠት ነው፤ ስነ-ምግባራችን በመበላሸቱ እና ሞራራችን በመውደቁ ምክኒያት ባልተገባ መንገድ ለመበልፀግ ባለ ፍላጎት ነው፤ ስለሆነም ስራው መጀመር ያለበት ከታች ነው:: ቤተሰብና የኃይማኖት ተቋማት ስነ-ምግባርን በመገንባት፣ በመግራት እና ተገቢ የሆነውን ፀባይ ይዘው ልጆች እንዲያድጉ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ናቸው፤ ስለሆነም የኃይማኖት ተቋማት የሚጫዎቱት ሚና እንደ ሚዲያ ተቋማት ከፍተኛ ነው:: በሀገራችን ያለው ችግር ሙስናን የሚታገለው መንግስት ብቻ አድርጎ የመመልከት ዝንባሌ ነው፤ መንግስት በውስጡ በጣም ብዙ ሌቦች ያሉበት፣ በበርካታ ችግሮች የተጠመደበት፣ በጣም ብዙ አጀዳዎችና ከዚም ከዛም የሚያዋክቡ በርካታ የፀጥታ ችግሮች እንዲሁም የሰላም መደፍረስ ያለበት በመሆኑ የሰው ህይዎትን ወደ የመታደግ ስራ በሚያከናውንበት ወቅት ሙሰኞች ጊዜ ያገኛሉ::

መንግስት ሙስናን በመታገል ረገድ ከሞላ ጎደል አቅሙ ይዳከማል ማለት ነው፤ ነገር ግን እንደ የኃይማኖት እና ሚዲያ ተቋማት ያሉ ተቋማት ከሌሎች ስራዎቻቸው በተጨማሪ ሙስናን የእለት ከእለት ስራቸው ማድረግ ይችላሉ::

የኃይማኖት ተቋማት ብዙ አማኞች በመኖሩ ስነ-ምግባር ከመገንባትና ሙስናን በመከላከል ረገድ ምቹ ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ አብዛኛው ኃይማኖተኛ ነው፤ ኃይማኖት የሌለው ዜጋ ብዙም አይደለም:: ስለሆነም ወደ ቤተ እምነቶችና መስጊዶች የሚመጡ መዕምናቸውንና ተከታዮቻቸውን ከስርቆት እንዲቆጠቡ፣ መፅሃፍ ቅዱስ ላይ ያሉትን አስርቱ ትዛዛት የሚባሉትን አትስረቅ፣ አታመንዝርና የሰው ገንዝብ አትመኝ የሚሉትን ትዛዛት በሁሉም መስከ ያሉ ስለሆነ ትዛዛቶችን በአግባቡ እንዲፈፀሙ መዕምኖቻቸውን መምከር፣ ማስተማር መገሰጥ ይገባቸዋል::

የኃይማኖትና የሚዲያ ተቋማት ስነ-ምግባር ከመገንባትና ሙስናን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ሚና ያላቸው በመሆኑ ሚናቸውን በሚወጡበት ደረጃ ላይ አጀንዳ ተሰጥቷቸው በአጀንዳው ልክ እየሰሩ አይደለም:: በሌላ መልኩ ራሳቸው ወደ ችግሩ እየገቡ ይታያልና ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ኮሚሽኑ፣ መንግስትና ባለድርሻ አካላት እንዲሁም የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ ሚናውን መጫዎት አለበት ብዬ አምናለሁ::

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡- በሀገራችን የሙስናና ብልሹ አሰራር ስራዎችን ለማከናወን አስቸጋሪ ናቸው ብለው የሚያስቡት ነገር ይኖር ይሆን?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- ሙስና በከፈተኛ ጥበብ የሚፈፀም፣ በከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትና ገነዘብ ባላቸው ኃይሎች የሚፈፀም በመሆኑ ውስብስብ ነው፤ ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ ትግሉ የሚያስተባብሩ አካላት ደግሞ ቅንጅት የላቸውም:: ሙስናን መታገል ቅንጅት ይጠይቃል፤ የሃይማኖትና የሚዲያ ተቋማት፣ የህግ አካላት በተለይ ምርመራና ክስ የሚመሰርቱ በኃላም ደግሞ ወደ ፍርድ ቤት ሂደው ፍርድ የሚሰጡ አካሎች ቅንጅት ላይ መላላት ይታያል::

ለምሳሌ፡- ሙሰኞች ከተከሰሱ በኃላ በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ምክኒያት ነፃ ነህ ተብለው የሚለቀቁ በርከት ያሉ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን፤ የተዘረፉ ሀብትም ባክኖ ይቀራል፤ ስለሆነም መንግስት ሁለት ሶስት ጊዜ ይጎዳል፤ የዚህ ሁሉ ምክኒያት የቅንጅት ችግር ነው::

ሙሰኞች በመቀናጀት፣ በመደራጀትና ትስስር በመፍጠር መረጃ የሚወጣባቸውን በልዩ ልዩ መንገድ አፍነው በመተባበር ሙስና ይፈፅማሉ፤ ሙስና የሚከላከሉትን የመንግስት አካላት ደግሞ ከህብረተሰቡ ጋር ቅንጅት የላቸውም:: ስለሆነም በየራሳቸው ታጥረው ስለሚታዩ አንዱ ችግር ነው ብዬ እገምታለሁ::

ሌላው ነባራዊ ሁኔታ የሚፈጥረው ችግር ነው፤ መንግስት ሽግግር ላይ በሚሆንበት ጊዜ ፀጥታ የማስከበርና የሰው ህይዎት የማዳን ስራ ላይ ቅድሚያ ትሰጣለህ:: ከሰው ህይዎት በላይ የሚቀድም ስለሌለ ማለት ነው:: በዚህ ምክኒያት ለሙሰኞች ነባራዊ ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው::

በሌላ በኩል መንግስት በኢኮኖሚው ላይ ያለው ተሳትፎ በመንግስት ውስጥ ሙስና ለሚፈፅሙ ሰዎች አመቺ መሆኑ አይቀርም፤ ምክኒያቱም አብዛኞቹ አገልግሎቶች በመንግስት የሚሰጡ ይሆናሉ:: በዚህ ረገድ መሳሪያዎቻችን ጠንክር ያሉ ካልሆኑ ሙስና ለሚፈፅሙ ሰዎች እድል መክፈቱ አይቀርም::

ሶስተኛው የምርመራ አቅማችን ያልተጠናከረ መሆኑ ነው፤ የሙስና መከላከል፣ የመመርመር እና የክስ አቅማችን ያልተጠናከረ መሆኑ እንዲሁም የተዘረፈ ሀብታችን ለማስመለስ ጠንክር ያለ ስርዓት የሌለን መሆኑ ለሙስና ትግሉ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥሩ ናቸው ብዬ አምናለሁ:: ችግሩን በመፍታትና አቅም መገንባት ይገባል፤ በተለይ ምርመራ ከፍተኛ ጥበብን የሚጠይቅ

መንግስት የሥነምግባርና... ወደ ገጽ 10 የዞረ

# ሳይቃጠል በቅጠል

## ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሠራር በጸዳ መልኩ መከናወን አለባቸው!!

**ተስፋዬ ሻሜቦ**

ዓለም ባንክ የሀገራችንን ልማት ለማሳደግ እንዲያግዝ ብድርና ዕርዳታ እንደሚሰጥ ይታወቃል:: ሀገራችን ከዓለም ባንክ በብድርና በዕርዳታ የምታገኛቸውን ገንዘቦችንና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ የዜጎችን ህይወትና ኑሮ የሚለወጡ ተግባራትን በትጋት ታከናውለች:: በተለይም ፕሮግራሞቹን እንዲያከናወኑ የተፈቀደላቸው ተቋማት ለፕሮግራም መሳካት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በተጠቃሚ ህብረተሰብ ጥያቄና ፍላጎት መነሻነት ትክክል ስለመሆኑ በራሱ ህብረተሰብ ተሳትፎ ጭምር በማረጋገጥ በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋሉ:: የተቀረጹ ፕሮጀክቶች በተያዘለቸው በጀትና ጊዜ በጥራት እንዲከናወኑና በአፈፃፀም ሂደት ውስጥ ሙስና እና ብልሹ አሠራር እንዳይከሰት እንዲሁም ተጠቃሚው ህብረተሰብ በፕሮጀክት አፈፃጸም ሂደት በሚደረገው ተሳትፎ ያሉትን ጥቆማዎች እንዲያቀርብ ሁኔታዎች ማመቻቸት የሚጠበቅባቸው ነው::

ፕሮጀክቱን በበላይነት የሚስተባብረው ተቋም የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችን በየፕሮጀክቶች ማደራጀት፣ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል የሥራ ቦታዎች ምቹ ማድረግ፣ ለሥራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሟላት ግዴታው ነው:: በተደራጀው መዋቅር የተመደቡት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎችም የተመቻቸለቸውን የሥራ ቦታ በመጠቀም ህብረተሰቡ ተጠቃሚ በሚሆንባቸው ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ሂደቶች ላይ ሊፈፀሙ የታሰቡ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ወይም በተፈጸሙ የሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮች ላይ ጥቆማዎችን እንዲያቀርብ የተለያዩ የጥቆማ ቅበላ አሰራሮች ( የነፃ ስልክ አገልግሎትና የዲጂታል ጥቆማ መቀበያ) በመዘርጋትና ለጥቆማ አቅረቢ ህብረተሰብ የማስተዋወቅና ግንዛቤ የመፍጠር ተግባር መፈጸም ይጠበቅባቸዋል::

እንዲሁም ከህብረተሰቡ የሚቀርቡ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን የመቀበል፣ የመመዝገብና ቀላል የሆኑ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን የማጣራት እና ከባድ የሙስና መረጃ ጥቆማዎች የመመርመርና የመክሰስ ሥልጠን ለተሰጠው አካል መላክና አፈፃፀሙን በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል:: ከቀረቡት የሙስና መረጃ ጥቆማዎች ውስጥ ሊፈጸም የታሰበ የሙስና ድርጊት ካለ ደግሞ ለተቋም የበላይ ኃላፊ በማሳወቅና በማማከር የማጣራት ሥራ በመሥራት የማሻሻያ ሀሳብ የማቅረብ፣ ሊፈጸም በታሰበው የሙስና ድርጊት ላይ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በተቋም የበላይ ኃላፊ በኩል ተቀባይነት ካለገኘ ጉዳዩን ለኮሚሽኑ የማመልከት ሥራዎች በትኩረት መሥራት ይጠበቃል::

ሌላው በሙስና መረጃ ጥቆማ ላይ ጥራት ያለውን ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል መላክ ነው:: የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ የቀረቡት የሙስና መረጃ ጥቆማዎች ብዛት፣ ማጣራት የተደረገባቸውና ውሳኔ ያገኙ የሙስና ጥቆማ መረጃዎችን እና መመርመርና መክሰስ ስልጠን ለተሰጠው አካል የተላኩ የሙስና መረጃ ጥቆማዎች መረጃዎች እንደአመጣጣቸው ቅደም ተከተል መሠረት በመያዝና በማደራጀት ለሪፖርት ተብሎ በተዘጋጀው ቅጽ መረጃዎችን በማስፈር ሪፖርት በጥራት ማዘጋጀትና ለክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ወይም የዘርፉ የፌዴራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ድረስ መላክ አለበት:: የክልል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንና የየዘርፉ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት የተላኩ የሙስና መረጃ ጥቆማዎችን በማደራጀትና ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ መረጃ ሪፖርት በማዘጋጀት ለፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን መላክ አለባቸው::

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ከክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች እና ከየዘርፉ የፌዴራል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የተላኩ ሪፖርቶችን እንደየፕሮግራሞች በማደራጀት በፕሮግራሙ ሥር የተከናወኑ ፕሮጀክቶች ከሙስና እና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ ተፈፃሚ ስለመደረጋቸው እስከ ፕሮጀክት ድረስ በአካል በመገኘት የማጣራት ሥራዎች ያከናውናል::

የማጣራት ሥራው የሚሠረው ከክልል ኮሚሽኖችና ፌዴራል ተቋማት የተላኩ መረጃዎች ምን ያህል ተጨባጭና ትክክለኛ ስለመሆናቸው በዝርዝር በመገምገምና ሌሎች ተያያዥ ከሆኑ መረጃዎች በማመሳከር ነው::

የማጣራት ስራው በሚከተሉት ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡- በፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ሊከስት የሚችለው ሙስና እና ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የተደራጀ ስለመሆኑ፣ ለሥራው ምቹ የሥራ አካባቢ ስለመፈጠሩ፣ የሙስና መረጃ ቅበለ አሠራር መዘርጋቱን፣ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በፕሮጀክት አፈፃፀም ሊከስት ስለሚችለው ሙስና እና ብልሹ አሠራር በቂ ግንዛቤ መያዙን፣ የፕሮጀክት ተጠቃሚ ህብረተሰብ ከፕሮጀክት ዕቅድ ጀምሮ አፈፃፀም በቂ ግንዛቤ ያለው ስለመሆኑ፣ ከህብረተሰብ የሚቀርቡ የሙስና መረጃ ጥቆማዎች መረጃ በአግባቡ ተደራጅቶ የተያዘና የሚዘጋጀው ሪፖርት በተጨባጭ መረጃ የተደገፈና ወቅታዊ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን እንዲሁም የተዘጋጀው የሙስና መረጃ ጥቆማና የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ሪፖርት በወቅቱ ለሚመለከተው ስለመላኩ በዝርዝር የሚገመገም ነው::

የኢትዮጵያ መንግስት ከዓለም ባንክ ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት በአሁን ወቅት 7 ውጤት ተኮር ፕሮግራሞች በትግበራ ሂደት ላይ ሲሆኑ፥ ሁለት ፕሮግራሞች በዝግጅት ሂደት ላይ ይገኙሉ:: ውጤት ተኮር ፕሮግራሞቹ የኢትዮጵያ መንግስት የየዘረፉን የልማት ፍላጎት ለማገዝ በብድርና በዕርዳታ መልክ ተግባራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ:: ፕሮግራሞቹ በተለያዩ የመንግስት ቁልፍ የልማት ዘርፎች ዓለማቸውን እንዲያሳኩ ድጋፍ የሚያደርጉ ሲሆን፥ እነዚህም በጤና፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በውሃና ኢነርጅ፣ በፋይናንስ/ገንዘብ፣ በኢንቨስትመንት/ሥራ ዕድል ፈጠራ እና በከተማና መሠረተ ልማት ዘርፎች ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ::

የመንግስትና የዓለም ባንክ ትብብርና ስምምነት እያደገ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመምጣቱ የፋይናንስ ድጋፉም በዚሁ ልክ እያደገ መጥቷል:: ስለሆነም በእነዚህ ሰባቱ ውጤት ተኮር ፕሮግራሞች ከሶስት ቢሊዮን ዶላር በላይ የፋይናንስ ድጋፍ በስምምነት ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል:: ይህን አዳጊ ፊላጎት መሰረት በማድረግ የፌዴራል የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከዓለም ባንክ ጋር በህግ በተሰጣቸው ስልጣን ስር ለመተባበር እና አብሮ ለመስራት የመግባቢያ ስምምነት መስከረም 22/2004 ተፈራርሟል::

የመግባቢያ ስምምነቱ ዋና ይዘቶች የሚከተሉ ናቸው::

1. በሀገራችን ሕግ መሠረት ከባድ ወንጀል ወይም በዓለም ባንክ ቡድን ደንብ እና ፖሊሲ መሠረት ማዕቀብ/ቅጣት ሊያስከትሉ ከሚችሉ ተግባር ጋር በተያያዘ ማጭበርበርን እና ሙስናን ለይቶ ለማወቅ እንዲሁም ማስረጃ እና የመከላከል አስፈላጊነትን በተመለከተ (በፍላጎት ወይም በጥያቄ) እርስበርስ መረጃ መለዋወጥ፣
2. ሙስናን እና ማጭበርበርን ለመለየት፣ ለማረጋገጥ እና ለመከላከል እያንዳንዱ አካል በሚያደርገው ጥረት ተገቢ ሆኖ ሲገኝ በጋራ ለመስራት፣
3. የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለማስፈጸም በሚያደራጁት እና በሚያከናውኗቸው እንዲሁም የጋራ ጥቅም ሲሆኑ በሚችሉ ተዛማጅ ተግባራት ላይ በጋራ መሳተፍ፣
4. በሁለቱም አካላት ሥልጣን እና ኃላፊነት ውስጥ የሚኖሩ ምርመራዎችን እና ድርጊቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን እና የውሳኔ ሃሳቦችን መረጃ መለዋወጥ፣
5. ውጤታማ እና ሚስጥራዊ የመረጃ ልውውጥን ለማመቻቸት እና ለማፋጠን የግንኙነት ማዕከል መሰየም እና

የጋራ ስትራቴጂካዊ ዓላማን ለማሳካት እና ለትብብር ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች መለየትና ለዚህም በየጊዜው መገናኘት ናቸው።

የውጤት ተኮር ፕሮግራሞች በዓለም ባንክ ከፋይናንስ ስርዓቶች ውስጥ የተበዳሪውን የልማት ፍላጎት መሰረት በማድረግ የተቀረፁ በመሆናቸው በጣም ተመራጭ ሲሆኑ፥ የዝግጅት ሂደቱም አሳታፊ እና ጥናት ላይ የተመሠረተ ነው:: ስለሆነም በሀገራችን ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ውጤት ተኮር ፕሮግሞች አጠቃላይ ይዘት ዝርዝር መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል::

### ክፍል አንድ

1. የፕሮግራሙ ስም፡- የከተማ ተቋማት እና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮገራም (UIIDP)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ከተሞች ተቋማዊ አፈጻጸምን በማሳደግ የከተማ መሠረተ ልማቶችን፣ አገልግሎቶችን እና የአካባቢ ኢኮኖሚ ልማትን ማሻሻል እና ማስቀጠል ነው::
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- በከተሞች የዕቅድ እና በጀት ዝግጅት ሂደት የዜጎች ተሳትፎ ማሻሻል፣ በከተማ ደረጃ የገቢ መሰብሰብ ዓቅም ማሻሻል እና የተሻሻለ መሠረተ ልማት፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ኦፕሬሽን እና የጥገና ሥርዓቶች፤ የተሻሻለ የአካባቢ እና ማህበራዊ አስተዳደር እና ጥበቃዎች እንዲሁም የተጠናከረ የተጠያቂነት እና የቁጥጥር ስርዓቶች ናቸው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከመጋቢት 2010 እስከ ሰኔ 2015 ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- 600 ሚሊዮን ዶላር ነው።
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- የፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ 117 ከተሞች የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎች ናቸው።
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቨሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋናዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- ማህበራትን በማደራጀት ሂደት ውስጥ በህጉ ያልተፈቀዱላቸው አባላትን አካቶ ማደረጃት፣ በጨረታ ሂደት ውስጥ የተጫራቾችን መረጃዎች በአግባቡ ያለመመርመር፤ ለማይገባው ተወዳዳሪ አዋርድ መስጠት እና በሂደቱም የጥቅም ተጋሪ መሆን፣ የፕሮጀክቶች የጥራት መጓደልና በጊዜ ያለመጠናቀቅ፣ የግንባታ ስፍራን ከመሠረተ ልማት እና ከይገባኛል ጥያቄ በወቅቱ ነፃ ያለማድረግ፣ የካሳ ክፍያ በወቅቱ ለሚገባው ያለመፈፀም እና ሕብረተሰቡን በበቂ ሁኔታ ያለመሳተፍ ናቸው።

### ክፍል ሁለት

1. የፕሮግራሙ ስም፡- ፍትሐዊ መሠረታዊ አገልግሎቶች ለጋራ ብልፅግና ፕሮግራም (ESPES)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- የመሠረታዊ አገልግሎቶችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማሻሻል እና የተጠያቂነት ስርዓቶችን ባልተማከለ ደረጃ ማጠናከር ነው።
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- የመሠረታዊ አገልግሎቶችን ፍትሃዊ ተደራሽነት ማረጋገጥ፣ በዜጎች ተሳትፎ የአካባቢ እና ማህበራዊ አስተዳደር አቅምን ማሳደግ፣ የመሠረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ታማኝነት ገጽታዎችን ማጠናከር እንዲሁም ጥራት ያለው መረጃ ተደራሽነት እና ውጤቶችን ማረጋገጥ ናቸው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከመስከረም 2008 እስከ ግንቦት 2016 ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- ለዋና ፕሮግራም 600 ሚሊዮን ዶላር፤ ለተጨማሪ ድጋፍ (የመጀመሪያ 700 እና ሁለተኛ 250 ሚሊዮን ዶላር)፤ በአጠቃላይ 1.6 ሚሊዮን ዶላር ነው::
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- በሀገራችን በሁሉም ወረዳ የሚገኙ 20% ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ናቸው።
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቨሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- ስለ ፕሮግራሙ በታችኛው መዋቅር (ወረዳ) ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን፣ የስነምግባር ባለሙያ በበቂ ሁኔታ ያለመመደብ፣ ከፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ የሙስናና ብልሹ አሠራር ሪፖርቶችን መዝግቦ ሪፖርት ያለመድረግ እንዲሁም የፕሮግራሙ የፋይናንስ ድጋፍ በክልል ደረጃ ካልሆነ በስተቀር በወረዳ ደረጃ ከመደበኛ ተለይቶ የማይታወቅ በመሆኑ የፕሮግራሙን ከሙስናና ብልሹ አሠራር አንጻር አፈጻጸሙን ለመገምገም አስቸጋሪ ማድረጉ የሚጠቀሱ ናቸው::

### ክፍል ሶስት

1. የፕሮግራሙ ስም፡- የአየር ንብረት እርምጃ በመሬት ገጽታ አስተዳደር ፕሮግራም (CALM)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- ዘላቂ የመሬት አያያዝ አሰራሮችን ማሳደግ እና ደህንነቱ የተጠበቀና ዘመናዊ የገጠር መሬት ይዞታ ባለቤትነት ተደራሽነትን ማስፋት ነው።
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- አሳታፊ የተፋሰስ አስተዳደር እና የገጠር መሬት አስተዳደር ነው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከ2012 እስከ 2016 ዓ.ም ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- 500 ሚሊዮን ዶላር ነው።
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- በሀገራችን በፕሮግራሙ በአሳታፊ የተፋሰስ ልማት እና ዘመናዊ የገጠር መሬት አስተዳደር ሂደት የታቀፉ ከ600 በላይ የወረዳ ነዋሪዎች ናቸው::
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቨሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- የስነምግባር ባለሙያ በበቂ ሁኔታ ያለመመደብ፣ የፕሮግራሙን ፋይናንስ ለሌላ ዓላማ ማዋል፣ የፕሮግራሙን ፋይናንስ በሚመዘብሩት ላይ አስተማሪና ህጋዊ እርምጃ ያለመውሰድ፣ ስለ ፕሮግራሙ በታችኛው መዋቅር(ወረዳ) ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን እንዲሁም ከፕሮግራሙ ጋር የተያየዙ የሙስናና ብልሹ አሠራር ሪፖርቶችን መዝግቦ በበቂ ሁኔታ ሪፖርት ያለመድረግ ናቸው።

### ክፍል አራት

1. የፕሮግራሙ ስም፡- አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም ለፍትሃዊነት (GEQIP-E)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- የውስጥ ቅልጥፍናን እና ፍትሃዊ ተደራሽነትን በማረጋገጥ አጠቃላይ የትምህርት ጥራትን ማሻሻል ነው።
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- የውስጥ ቅልጥፍናን፣ ፍትሃዊ ተደራሽነትን እና ጥራትን ማሻሻል እንዲሁም የዕቅድ፣ የፖሊሲ ቀረጻ እና የሪፎርም ሥራዎችን ሥርዓት ማጠናከር ናቸው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከሚያዝያ 2009 እስከ ሀምሌ 2014 ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- 574.6 ሚሊዮን ዶላር ነው።
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- በመላ ሀገራችን በየአመቱ 27 ሚሊዮን ተማሪዎችን፣ 520,000 መምህራንን እና 35,000 የመንግስት አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን (0-ክፍልን ጨምሮ) ተጠቃሚ ለማድረግ የተቀረፀ ፕሮግራም ነው::
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቨሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- የስነምግባር ባለሙያ በበቂ ሁኔታ ያለመመደብ፣ የፕሮግራሙን ፋይናንስ ለሌላ ዓላማ ማዋል፣ የፕሮግራሙን ፋይናንስ በሚመዘብሩት ላይ አስተማሪና ህጋዊ እርምጃ ያለመውሰድ እና በሙስና ወንጀል ሊያስጠይቁ የሚችሉትን ጉዳይች በአስተዳደራዊ ሁኔታ ታይቶ እንዲታለፍ ማድረግ እንዲሁም ከፕሮግራሙ ጋር የተያየዙ የሙስናና ብልሹ አሠራር ሪፖርቶችን መዝግቦ በበቂ ሁኔታ ሪፖርት ያለመድረግ ናቸው።

### ክፍል አምስት

በዓለም ባንክ ... ወደ ገጽ 10 የዞረ

# ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሠራር...

1. የፕሮግራሙ ስም፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራም (ELEAP)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነትን ለማሳደግ እና የመንግስትን የኤሌክትሪፊኬሽን መርሃ ግብር የማቀድ እና የመተግበር ተቋማዊ አቅምን ማሳደግ ነው።
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- በኤሌክትሪክ ኃይል መስመር በተሸፈኑ ቦታዎች ላይ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ማሳደግ፣ ከኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ውጪ ሌሎች ተጨማሪ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ማሳደግ እና የዘርፉን አቅም እና ተቋማዊ ማሻሻያ ማጠናከር ነው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከየካቲት 2010 እስከ የካቲት 2015 ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- 375 ሚሊዮን ዶላር ነው።
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- በሀገራችን ከ500 በላይ የሚሆኑ የኤሌክትሪክ አገልግሎት መስጫ ማዕከሎች ተጠቃሚ ማሕበረሰብ (ሪጅን እና ዲስትሪክትን ጨምሮ) ናቸው።
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቬሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- የስነምግባር ባለሙያ በበቂ ሁኔታ ያለመመደብ በተለይ በዲስትሪክትና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ደረጃ፣ አገልግሎትን በፍትሐዊነት ያለመስጠት (ቅደሚያ ያመለከተ ቅድሚያ ማግኘት) ሲገባው የተለየ ጥቅም ፍለጋ ሌሎችን ማስቀደም፣ ተቋሙ ለሚሰጠው አገልግሎት ከህግ እና ደንብ ውጭ ክፍያ መጠየቅ (አዲስ ሀይል ለማግኘት፣ ብልሽት ለማስጠገን እና ሌሎችም)፣ ያለተቋሙ ዕውቅና አገልግሎቶችን ከደንበኞች ጋር በመመሳጠር የግል ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ለማይገባቸው አግልግሎት መስጠት እና ደንበኛን ማጉላላት (ማመላለስ) እንዲሁም በሙስናና ብልሹ አሠራር በሚጠረጠሩ ባለሙያዎች ላይ አጣርቶ አፋጣኝ እርምጃ ያለመውሰድ ተጠቃሽ ግኝቶች ናቸው።

### ክፍል ስድስት

1. የፕሮግራሙ ስም፡- የጤና ዘላቂ ልማት ግቦች ፕሮግራም (HSDGP)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- አጠቃላይ የእናቶች እና ህጻናት ጤና (MCH) አገልግሎት አሰጣጥ እና አጠቃቀምን ማሻሻል ነው።
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- የቅድመ ወሊድ አገልግሎት ሽፋን ማሳግ፣ በሰለጠነ የጤና ባለሙያ ክትትል የወሊድ ሽፋን ማሳደግ እና ከ12-23 ወራት ለሆኑ ህጻናት የPentavalent የክትባት ሽፋን ማሳደግ እንዲሁም የወሊድ መከላከያ ስርጭት መጠን ማሳደግ ናቸው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከየካቲት 2005 እስከ ሰኔ 2010 ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- 350 ሚሊዮን ዶላር ነው።
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- በሀገራችን የጤና ዘርፍ አገልግሎት ተጠቃሚ ማህበረሰብ (በ19 የኢትዮጵያ መድሃኒት አቅርቦት ኤጅንሲ አማካኝነት) ነው።
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቬሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- ከፕሮግራሙ ጋር የተያየዙ የሙስናና ብልሹ አሠረር ሪፖርቶችን መዝግቦ በበቂ ሁኔታ ሪፖርት ያለመድረግ፣ መድሃኒት በማጓጓዝ ሂደት ላይ በአግባቡ የሚፈለገው ቦታ ላይ ተደራሽ ያለመሆን፣ የመጫንና የማውረድ ሂደቱ ለብልሹ አሠራር ተጋላጭ መሆኑ እና የጤና ተቋማት ባቀረቡት ፍላጎት መሠረት መድሃንት የማይደርሳቸው መሆኑ እንዲሁም መድሃንቶችን በወቅቱ ያለማሰራጨት ናቸው።

### ክፍል ሰባት

1. የፕሮግራሙ ስም፡- የኢኮኖሚ ዕድሎች ፕሮግራም (EOP)፥
2. የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ፡- ዘላቂ በሆነ መንገድ ለኢትዮጵያውያን እና ለስደተኞች አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ማቅረብ ነው።
3. ከፕሮግራሙ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- በመደበኛነት መሥራት ለሚችሉ ስደተኞች የሥራ ስምሪት እና የተሻሻለ የሥራ ገበያ መፍጠር፣ በኢንቨስትመንት መስህብ ለኢትዮጵያውያን የተፈጠሩ ኢኮኖሚያዊ እድሎች፣ በአለም አቀፍ ገዥዎች እና በአገር ውስጥ አቅራቢዎች መካከል ያለው ትስስር እና የተሻሻለ የመንግስት ስራ ስምሪት አገልግሎት እንዲሁም የተሻሻለ የሰው ኃይል ምርታማነት፣ የስራ ጥራት፣ የአካባቢ እና ማህበራዊ ተገዢነት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የሰራተኛ ደረጃዎችን እና የስራ ሁኔታዎችን ለመከታተል እርምጃዎችን መውሰድ ናቸው።
4. የፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ፡- ከሀምሌ 2010 እስከ ሰኔ 2017 ሲሆን፥
5. የፕሮግራሙ በጀት፡- 259.3 ሚሊዮን ዶላር ነው።
6. የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ማህበረሰብ፡- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የስደተኞች እና የስደት አገልግሎት፣ የኢንዱስትሪ፣ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን እና የሥራና ክህሎት ሚንስቴር እንዲሁም ኢንዱስትሪ ፓርኮች(ሀዋሳ፣ ቦሌ ለሚ እና ኮምቦልቻ ናቸው)።
7. በአፈጻጸም ሂደት ላይ በተካሄዱት የቬሪፊከሽን ሥራዎች የቀረቡ ዋና ዋና የሙስናና ብልሹ አሠራር ግኝቶች፡- የስነምግባር ባለሙያ ያለመመደብ፣ ስለ ፕሮግራሙ በታችኛው መዋቅር (በፓርኮች ደረጃ) ያለው ግንዛቤ እጅግ ዝቅተኛ መሆን እና ከፕሮግራሙ ጋር የተያየዙ የሙስናና ብልሹ አሠራር ሪፖርቶችን ያለመመዝገብ ናቸው።

በውጤት ተኮር ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዙሪያ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በመከላከል ፕሮግራሞቹ የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ በቀጣይ የሚከተሉ ጉዳዮች ትኩረት የሚሹ ናቸው።

በፕሮግራሙ የታችኛው መዋቅር/በወረዳ/ከተማ አስተዳደር/አገልግሎት መስጫ ማዕከላት/ኢዱስትሪ ፓርኮች/ በቂ የስነምግባር ባለሙያ መመደብና ስለ ፕሮግራሙ አስፈላጊወውን ግንዛቤ ማስጨበጥ፤ የቀረቡ ሙስናና ብልሹ አሠራር ቅሬታና አቤቱታ ጉዳዮች በየወቅቱ መመዝገብ እና ለሚመለከተው ማሳወቅ፤ በሂደት ላይ ያሉ (ውሳኔ ያላገኙ) በፕሮግራሙ የቀረቡ የቅሬታና አቤቱታዎችን ተከታትሎ ውሳኔ ማስጠት፤ ሙስናና ብልሹ አሠራር ሂደት ተሳታፊ የሆኑ አካላት አስፈላጊውን ህጋዊ እርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤ በፕሮግራሙ አፈጻጸም ሂደት ላይ አስፈላጊውን ግንዛቤ ለተጠቃሚ ማህበረሰብ እና ለታችኛው አስፈጻሚው አካል መፍጠር እና በፕሮግራሙ በየ6 ወሩ በኮሚሽናችን የሚሰጡ የቬርፊኬሽን ግኝቶች ላይ ትኩረት በመስጠት አፋጣኝ የእርምት እርምጃ በመውሰድ ማሳወቅ እንዲሁም በፕሮግራሙ አፈጻጸም ሂደት ላይ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ማሳተፍ እና ተቀናጅቶ መስራት፤ በፕሮግራሙ አፈጻጸም ሂደት ላይ አስፈላጊወን የቅሬታና አቤቱታ መቀበያ ሥርዓቶችን መዘርጋትና ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ማሳወቅ የሚሉት ዋና ዋና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።

# መንግስት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና...

ነው፣ ማስረጃ ማሰባሰብ ከፍተኛ እልህን የሚጠይቅ ነው፤ መሰዋትነትም ያስከፍላል፤ ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜም ይጠይቃል፤ ለዚህ የሚሆን በቂ ነገር ማድረግና ምርመራን ጠንከር አድርጎ ማስፈፀም ይገባል።

ሌላው ከምርመራ በፊት ሙስናን መከላከል እራሱ ከባድ ስራ ነው፤ ምክኒያቱም የሰዎችን አመለካከት መቀየር፣ ትውልድንና ዜጋን በመልካም ስነ-ምግባር መገንባት ነው። ይሄ ወቅት ገንዘብና ብዙ ስርዓቶችን መፍጠር የሚጠይቅ ነው፤ ስለሆነም ከተለመደው አካሄድ ወጣ ማለት ይጠይቃል። ስለዚህ ችግሮች ከተቃለሉ ሙስና እንደ ሌሎች ሀገሮች ሙሉ በሙሉ ማጥፋት ባችልም እንኳን የልማታችን፣ የሰላማችንና የዲሞክራሳችን ጠንቅ እንዳይሆን ማድረግ እንችላለን ማለት ነው።

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡-የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና የፍትህ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ምን መሆን አለበት ብለው ያስባሉ?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሻሻለው መቋቋሚያ አዋጅ ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር የመረጃ ቅብብሎሽ እንዲያረግና ሪፖርት እንዲቀበል እንዲሁም ተናቦ እንዲሰራ ስልጣንና ኃላፊነት ተሰጦታል። ይህን ስልጣንና ሃላፊነት ጠንከር አድርጎ መወጣት እና ለፀረ-ሙስና ትግሉ እንቅፋት የሚሆኑ የመንግስት አካላት ሲኖሩ ማጋለጥ፣ ለህብረተሰቡ ጉዳቱን ማሳየት፣ እና ህብረተሰቡ እንዲነሳሳ ማድረግ ነው። ከህብረተሰቡ ትግል ውጭ ሙስናን ወደ ምንፈልገው ደረጃ ማሻገር አይቻልም። ምክኒያቱም በህብረተሰቡ ውስጥ ጨለማን ተገን ተደርጎ የሚፈፀም የሙስና መንገድ ጉቦ ነው፤ ማጭበርበርና ማታለል ነው፤ እንደዚህ አይነት ሙሰና በህብረተሰቡ የሚፈፀሙ ናቸው፤ እነዚህን ችግሮች ራሱ ህብረተሰቡ እንዲያጋልጥ፣ እንዲታገልና እንዲያግዝም የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጠንከር ያለ አሰራርና አደረጃጀት መከተል ያለበት ይመስለኛል። በአዋጁ የተሰጡት ስልጣኖች አሉ፤ አስቼኳይ የሙስና መከላከል ስራ መስራት አለበት፤ በተለይ በግዥ ሂደቶች ላይ የሚታዩ ችግሮች በጣም ሰፋ ያሉ ናቸው፤ በጨረታ አዋጣጥ፣ ተጫራጮችን በማወዳደር ሂደት ግልፅነት የሚጎላቸው በጣም በርከት ያሉ አሰራሮች አሉን። አሁን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ጨረታን የማውጣትና የማወዳደር ዘዴ በመንግስት የተጀመረውን ሂደት ማጠናከር ይገባል። በተቻለ መጠን የሰው ጣልቃ ገብነት በልዩ ልዩ መንገድ እንዳይኖር መከላከል ነው። በተለይ በኢንተርኔት የሚደረጉ የሳይበር ትግሎችን ማጠናከር፣ የምንሰጣቸው አገልግሎቶች ከሰው ንክኪ የራቁ እንዲሆኑና በቴክኖሎጂ የተደገፉ በማድረግ ረገድ የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የተሰጠው ትልቅ ስልጣን ነው። ይህን ስልጣኑን ተግባራዊ በማድረግ ከእስካሁኑ በተለዬ መንገድ ጠንከር ብሎ ህብተሰቡን ማነሳሳትና ማታገል ይገባዋል።

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡-ኮሚሽኑን በአሰራርና በአደረጃጀት እንዲሻሻል ቋሚ ኮሚቴው ያከናወነው / ሊያከናውን ያሰበው ተግባር ይኖር ይሆን?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፤ በዚህ ልክ ማጠናከር ይገባል፤ ስራዎችን ማበረታታትና እስከመጨረሻው ማከናወን ይገባል። የሙስና መከላከል ተግባሩን ሲሰራ ተገቢ የሆነ ድጋፍ ማድረግ ይገባል። ሙስና የመከላከል ስራ የኮሚሽኑ ብቻ አድርጎ የማሰብ ችግር፣ የምርመራ ስራ የፖሊስ ብቻ አድረጎ የማሰብ፣ የክስ ስራ የአቃቢ ህግ ስራ ብቻ አድርጎ የማሰብ ችግሮች ይታያሉ። እነዚህ በጭራሽ አያዋጡም፤ በተናጠል የመቆም፣ የቸልተኝነትና የምንቸገረኝነት ነገር እየጎዳ ያለው የራሳችን ዜጎች ነው፤ እየተዘረፈ ያለው የኛው ሀብት ነው።

በዚህ ሁኔታ የኮሚሽኑ አደረጃጀትና አሰራር ተቋማዊ ሁኖ እንዲጠናከር የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጠንክሮ እየሰራ ነው። መንግስት ተቋሙን የበለጠ ማሻሻል አለበት ብለን እናስባለን። የተቋቋመው የፀረ-ሙስና ኮሚቴ ጊዜያዊ ኮሚቴ እንጂ ቋሚ አይደለም፤ ቋሚ ሁኖ ሙስናን ሊከላከል አይችልም፤ ዋናው የፌደራል የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን መገንባት ነው።

ስለሆነም መንግስት የስነ-ምግባርና የፀ-ሙስና ኮሚሽንን በአደረጃጀት፣ በአሰራርና በአቅም እንዲጠናከር አስፈፃሚውን አካል ግፊት በማድረግ፣ በመቆጣጠርና በመከታተል ረገድ የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሚናውን የሚወጣ ይሆናል። ብዙ መሻሻል ያሉባቸው ነገሮች እንዳሉም እናውቃለን።

የ«ፀረ-ሙስና» ጋዜጣ፡-በስነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ዙሪያ ለህዝቡ የሚስተላልፉት መልክት ምንድን ነው?

ክቡር እውነቴ አለነ፡- የስነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስናን የመከላከል ስራ የቅብብሎሽ ስራ ነው፤ ስራው የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው፤ ልጆች ከአስተዳደግ ጀምሮ በስነምግባር የተኮተኮቱ፣ ከፍተኛ የሞራል ደረጃን የተቀበሉ፣ ለአልተገባ የስነ-ምግባር ጉድለት እንዳይዳረጉ በማድረግ ረገድ ወላጆች የማይተካ ሚና አላቸው። ስራው ከቤተሰብ መጀመር ብቻ ሳይሆን ከህብረተሰቡ ወጣ ብለን አካባቢው ደግሞ ለአስተዳደግና ለስነ-ምግባር ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፆኦ አለው። እኛ ባደግንበት ዘመን እና ቀደም ብሎ የማንም ልጅ ይሁን የተበላሸ ስነ-ምግባር ሲያሳይ ማንም ተቆጥቶና ተገስፆ የመመለስ ነገር ነበር፤ አሁን ግን የምንቸገረኝና የግዴለሽነት፣ የኔምናገባኝነት ችግር ይበዛል። ስለዚህ በቤተሰብ፣ በህብረተሰቡና በአካባቢው የስነ-ምግባር ግንባታውን ካልደገፈ የህብረተሰቡ የአስተዳደግ ነገሩ ይበላሻል ማለት ነው።

አስተዳደጋችን ከተበላሸ ደግሞ በመጨረሻ ለብዙ ችግሮች እንጋለጣለን፤ በመጀመሪያ የምንጋለጠውም የስነ-ምግባር ውድቀት ነው። በዚህም በዛም በተገኘው መንገድ ሰርቶ መበልፀግ ሳይሆን ባልተገባ መንገድ መበልፀግ፣ ተራ ውንጀሎችን መፈፀም፣ አልባሌ ቦታዎች መዋልና የማንቆጣጠራቸው የስነ-ምግባር ጉድለቶች የመምጣት ነገር ይኖረዋል።

ስለዚህ ህብረተሰቡ እየተዘረፈ ያለው ገንዘብ የእኔ ነው፣ ጉዳት እየደረሰባቸው ያሉት ልጆች የኔ ናቸው፤ ነገም ከእኔ ላይ ነው ጉዳት የሚደርሰው ብሎ በሙስና መከላከልና መታገል ረገድ የማይተካ ሚናውን መጫወት አለበት፤ አያዋጣንም፤ እስካሁን "የሽ ገንዘብ ብላው የሽ ወንድምን አትካው" የሚል ብሂል አያዋጣም፤ እንደማያዋጣን አይተነዋል፤ እየተጎዳን ያለነው እኛው ነው።

እኛው የምንከፍለው ግብር ነው ሙስና የሚፈፀምበት፤ እኛ በነፃ የምናገኘውን አገልግሎት ነው ጉቦ የሚበሉበት፤ ስለሆነም ይሄ በጣም ጎድቶናል፤ ከዚህ በላይ ጉዳት ሊያደርስብን አይገባም። አሁን የሚታየው አገራዊ ምስቅልቅል፤ ለምናየው የፀጥታ እና የሰላም መደፍረስ፣ የነበሩት የማህበረሰቡ ማህበራዊ ግንኙነት የመበጣጠስ እና ማህበራዊ ስሪታችን የመበላሸት ነገር የመጣው በስነ-ምግባር ዝቅጠትና በሌቦች ምክኒያት በመሆኑ ህብረተሰቡ ሙስናን በመታገል ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርበታል። ከእስካሁኑ ካለው የበለጠ እንቅስቃሴ መደረግ አለበት።

በሌላ በኩል መንግስት በተለይም የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙና ኮሚሽን ይሁን ሌሎች የህግ አስከባሪ አካላት የፀረ-ሙስና ትግሉን በማስተባበር፣ በማቀናጀትና ተደጋግፎ መስራት ይገባቸዋል። መንግስት ቸልተኝነት ባሳየበት ጊዜ ህብረተሰቡ ደፍሮ መገሰፅ፣ መምከርና መቆጣጠር ይኖርበታል፤ የራሱ ችግር የሚጎዳው ራሱ ስለሆነ ሂዶ ሂዶ የራሱን ህይወት ጭምር እስከማጥፋት እየሄደ ነው። ስለሆነ ከዚህ አካባቢ ተገቢ የሆነ ክትትል እንዲያደርግ፣ እንገስጥና እንዲያሳፍራቸው ሊያደረግ ይገባል። በሌላ መልኩ ሙስና የሚታገሉ ሰዎችን ደግሞ የመደገፍ፣ አለዋችሁና አይዟችሁ እንዲል ማድረግ ይገባልና ለህብረተሰቡ ከምንሰራው ስራ በተጨማሪ ለኮሚሽኑና ለመንግስት መረጃ መስጠት የህብረተሰቡ ኃላፊነት ነው።

መንግስት እስካሁን ካለው አሰራር ወጣ ብሎ ለየት ያሉ አሰራሮችን መከተል አለበት፤ ሙስና ውስብስብብ ነው፤ እስካሁን በነበረው የትግል መንገድ ሙስናን ልንታገለውና ልንከላከለው አንችልም፤ እየሞከርነው ውጤታማ ሳይሆን የበለጠ ጉዳት እያመጣ ነው ያለው፤ መንግስት ሙስናን የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ መታገል አለበት፤ ተቋማዊ ማድረግ አለበት፤ የህግ አካልም ይሁን ሙስናን የመከላከል ሚና ያለውን የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአሰራርምና በአደራጃጀት ከፍተኛ ድጋፍ ማድረግ አለበት። የሚያስፈልገው የሰው ኃይል በጀት መመደብና የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ማመቻቸት አለበት የሚል መልክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ።

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

## በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር የመደበኛ ወንጀሎችንና የሙስና ወንጀሎችን በፍርድ ቤት የማስረዳት ሸክም ወይም ሀላፊነት ምን ያህል ያውቃሉ?

የተለያዩ የዓለማችን ሀገራት ለህልውናቸውና ለሠላማቸው፥ ለእድገትና ብልፅግናቸው እጅግ አደገኛ እንቅፋት አድርገው ከሚወስዷቸውና በጥብቅ ከሚከላከሉት የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ የሙስና ወንጀል አንዱና ዋናው ነው። የዚህ ወንጀልም ባህሪ ከሀገራት አልፎ ድንበር ተሻጋሪና የሁሉም ሀገራት ህዝቦችና መንግስታት የጋራ ችግር መሆኑን በመረዳት በጋራና በተናጠል ለመከላከል የተለያዩ እርምጃዎችን የወሰዱ ሲሆን፥ ወንጀሉን ቀድሞ ከመከላከል በተጨማሪ ጠበቅ ያለ የመመርመርና የመክሰስ ስራ በመስራት ወንጀለኞች ለፈፀሙት የሙስና ወንጀል ተግባር እንዲጠየቁና በሙስና የመዘበሩትንም ሀብት እንዲመልሱ ከመደበኛው የወንጀል ሥነ ሥርዐትና አካሄድ ወጣ ባለ ሁኔታ የተለያዩ ስልቶችን ይከተላሉ:: ከነዚህም ውስጥ ብዙ ሀገራት የሙስና ወንጀል እጅግ ውስብስብና ስልጣን፣ ገንዘብ፣ ሀብት እና ዕውቀት የረቀቀ ኔትዎርክ ባላቸውና በስውር ሠንሰለት በተደራጁና ቀድመው አስበውበትና በረቀቀ ጥናት የወንጀል ድርጊታቸው እንዳይታወቅ ሁሉንም አይነት የማስረጃ መንገድ ቀድመው በተጠና ሁኔታ አመቻችተው የሚፈፅሙት በመሆኑ የሚፈፅሟቸውን የሙስና ወንጀሎች ከእነሱ በቀደመ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ የመመርመር፣ የመክሰስና በፍርድ ቤት አቅርቦ በተሟላ ሁኔታ ለማስረዳት በጣም አስቸጋሪ መሆኑን በመረዳት የተለያዩ ሀገራት በየሀገራቸው የወንጀል ፍትህ ሥርዐት ውስጥ የሙስና ወንጀልን ከመደበኛው ወንጀል በተለየ ሁኔታ መመርመርና በፍርድ ቤት በማስረዳት ዙሪያ የተለያዩ የሥነ ሥርዐት ህጎችን በማውጣት እየተገበሩ ይገኛሉ::

ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚህ ችግር ተጋላጭና የወንጀል ፍትህ ስርዐቷም በተለይ በሙስና ወንጀል ምርመራና ክስ ዙሪያ ወንጀለኞች የሚፈፅሙትን የሙስና ወንጀል በብቃትና በዘመናዊ ዕውቀትና ቴክኖሎጂ ማስረጃዎችን አደራጅቶ ለፍርድ በማቅረብና በማስረዳት ዙሪያ ከፍተኛ የዓቅምና የቴክኖሎጂ ውስንነት ስላለባት፥ ይህን ችግር በተቻለ ዓቅም ለመቀነስ የተለያዩ ህጋዊና ተቋማዊ እርምጃዎችን የወሰደች ሲሆን፤ በዋናነት ልዩ የሙስና ወንጀሎች ምርመራ ሥነሥርዐት ህግ ከመደበኛው የወንጀል ሥነሥርዐት በተለየ ሁኔታ በአዋጅ አውጥታ እየተገበረች ትገኛለች::

በዚህም የሙስና ወንጀል ምርመራ ልዩ የሥነሥርዐት ህግ አንዱና ልዩ ሁኔታው በመደበኛው ወንጀል ሥነሥርዐት ዓቃቤ ህግ የወንጀል ክስ ከመሠረተ በኋላ ተከሳሽ ወንጀል ስለመፈፀሙ በፍርድ ቤት ከከሰሰ በኋላ ወንጀሉን ለፍርድ ቤት ከበቂ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ሸክም ወይም ሀላፊነት /burden of prove beyond reasonable doupt / የከሳሽ ዓቃቤ ህግ ሲሆን፤ በዚህ የሙስና ወንጀሎች ልዩ የሥነ ስርዐት ህግ ግን የማስረዳት ሸክም ከዓቃቤ ህግ ወደ ተከሳሽ እንዲዞር የተደረገ ነው። የዓቃቤ ህግ ሀላፊነትም ተጠርጣሪው የሙስና ወንጀል ስለመፈፀሙ በተለያዩ መንገዶች በማስደገፍ ክስ መመስረት ሲሆን፣ ለምሳሌ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት አፍርተሃል ወይም ከገቢህ በላይ ሀብት አፍርተሃል ብሎ ተጠርጣሪ ያፈራውን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ወይም ከሚያገኘው ገቢና ወርሀዊ ደመወዝ ጋር የማይመጣጠን ሀብት አፍረተሀል በማለት እስካሁን ሲያገኝ የነበረውን ህጋዊ ገቢና አሁን ያካበተውን ሀብት አስልቶና በሌሎች የሠውና የሠነድ ማስረጃዎች አደራጅቶ ክስ ለፍርድ ቤት የማቅረብ ሀላፊነት ብቻ ዓቃቤ ህግ ሲኖርበት እንደ መደበኛው ወንጀል ዓቃቤ ህግ ከበቂ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ሸክም በሙስና ወንጀል ወደተከሳሽ እንዲዞር የተደረገ ሲሆን እና ተከሳሽም ዓቃቤ ህግ ያቀረበብኝ ክስ ሀሰተኛ ነው በማለት የማስረዳት፣ የማረጋገጥና ክሱን ውድቅ የማድረግ ሀላፊነት ያለበት ሲሆን፣ እነዚህን ሀብቶችና ገንዘቦች ያፈራሁት በህጋዊ መንገድ ነው ብሎ ማስረዳት ካልቻለ ያፈራው ቋሚም ሆነ ተንቀሳሻና ገንዘቦች ሌሎችም በሙስና ወንጀል የተገኙ ስለሚሆን የሙስና ወንጀል ጥፋት ተጠያቂ ከመሆን ባለፈ ሁሉም ሀብቶች ተወርሰው ለመንግስት ገቢ እንዲሆኑ ይደረጋል::

የሙስና ወንጀል የምርመራ ውጤቶችና ሂደታቸው እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ አባል እንደሆነ በማስመሰል እና በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 9 አራራት ሆቴል አካባቢ ያለው አምስት ሺህ ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ በከተማው ካቢኔ በምደባ አስወስንልሀለሁ በማለት የማታለል ወንጀል የፈጸመው አቶ ፍቅረስላሴ ታደሰ እና ግብራአበሮቹ በቁጥጥር ስስር ውለው ምርመራ እየተካሄደባቸው ይገኛል።

ግለሰቡ 30,000,000 ብር ቅድመ ክፍያ ትከፍላለህ ብሎ በማሳመን የግል ተበዳይ ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዳያድርበት ለማድረግ በተለያየ ጊዜ የተፈረሙ ሰነድ በማስመሰል እና ራሱን የአዲስ አበባ የመሬት ልማትና የመልካም አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ በማድረግ ሀሰተኛ ቲተርና ክብ ማህተሞችን በማዘጋጀት የተለያዩ ደብዳቤዎች ላይ በመፈረም ደብዳቤዎች ለግል ተበዳዩ በማሳየት የማሳመን ስራ ሲያከናውን ቆይቷል::

በጋራ በጥቅም በመመሳጠር 1ኛ ተጠርጣሪ አቶ ፍቅሬ በየነ የተባሉትን መሬት መግዛት እንደሚፈልግ ካረጋገጠ በኋላ እራሱን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ አባል እንደሆነ እና በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 9 አራራት ሆቴል አካባቢ ያለው አምስት ሺህ ካሬ ሜትር ባዶ ቦታ በከተማው ካቢኔ በምደባ አስወስንልሃለሁ በማለት ለዚህም 30,000,000 ብር ቅድመ ክፍያ ትከፍላለህ ብሎ በማሳመን የግል ተበዳይ ምንም አይነት ጥርጣሬ እንዳያድርበት ለማድረግ በተለያየ ጊዜ ካቢኔዎች የፈረሙመበት ሰነድ በማስመሰል እና ራሱን የአዲስ አበባ የመሬት ልማትና የመልካም አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ በማድረግ ሀሰተኛ ቲተር እና ክብ ማህተቦችን በማዘጋጀት የተለያዩ ደብዳቤዎች ላይ በመፈረም፣ ደብዳቤዎቹን ለግል ተበዳዩ በማሳየት፣ 2ኛ ተጠርጣሪ ታምራት እስጢፋኖስ ወደ ሚሰራበት ቢሮ ይዞት በመሄድ ከሁለተኛ ተጠርጣሪ ጋር በማስተዋወቅ፥ ሁለተኛ ተጠርጣሪም በሀሳቡ ሙሉ በሙሉ በመስማማት የግል ተበዳይን ጉዳዩ ቀላል እንደሆነና በቀላሉ ሊያስወስኑለት እንደሚችሉ በማሳመን የግል ተበዳይን የተለያዩ ሰነዶች እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ 1ኛ ተጠርጣሪ ፍቅረስላሴ ታደሰ የበለጠ የግል ተበዳዩ ላይ እምነት እንዲያድርበት በማሰብ ወደ 3ኛ ተጠርጣሪ ዘውዱ ደገፋ የተባለው ግለሰብ ወደ ሚሰራበት የካ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ቢሮ በመውሰድ በማገናኘት 3ኛ ተጠርጣሪም በተመሳሳይ በጉዳዩ በመስማማት ቦታው ድረስ ሂዳ ልኬት እንድትፈጽም 4ኛ ተጠርጣሪ የሆነችውን ቃልኪዳን አክሊሉ የተባለቸዋን መሀንዲስ በመመደብ እና ልኬት እንዲወሰድ በማድረግ ጉዳዩን በቀላሉ ማስወሰን እንደሚችሉ በቀጥታ ለግል ተበዳይ በመናገር ከፍተኛ እምነት እንዲያድርባቸው ያደረጉ ሲሆን፥ 1ኛ ተጠርጣሪ በስምምነታቸው መሰረት በተለያየ ቀን የ8,250,000 ቼክ በመቀበል ተጠርጣሪዎች በጋራ በመሆን ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ምክንያት ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተካሄደባቸው ይገኛል።

በሌላ መረጃ "በፍርድ ቤት የተያዘ የሙስና ክስን እንዲቋረጥ አስደርጋለሁ" በማለት ጉቦ ተቀብሏል በተባለ ግለሰብ ላይ ክስ ተመሰረተ:: ክሱ የቀረበው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ነው።

ተከሳሽ ሳሙኤል ታደሰ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ነዋሪ መሆኑ እና በግል ሥራ ላይ መሰማራቱን በፍትሕ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የቀረበው ክስ አመላክቷል::

ተከሳሹ በመንግሥት ወይም በሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚገባውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ፥ በሙስና ወንጀል ተከሶ ጉዳዩ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 5ኛ የሙስና ጉዳዮች ችሎት እየታየ የሚገኝ ተከሳሽን "ክስ እንዲቋረጥ አስደርጋለሁ" በማለት ከተከሳሽ ቤተሰቦች ጉቦ መጠየቁ በክሱ ተገልጿል::

በየካቲት ወር 2015 ዓ.ም በአራዳ ክፍለ ከተማ ፒያሳ አካባቢ በሚገኝ ጎንደር ሆቴል ውስጥ ከ1ኛ እና 2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር የግል ተበዳዮች ጋር በመገናኘት እምነት ለማግኘት አስቦ በሐሰት ዐቃቤ ሕጎችንና የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊዎችን እንደሚያውቃቸው በመግለጽ፥ "ክሱ እንዲቋረጥና ተከሳሹ ከስር እንዲፈታ አደርጋለሁ" በማለት ለማስፈጸሚያ 2 ሚሊየን ብር ጉቦ እንዲሰጡት መጠየቁን ክሱ አመላክቷል::

በግል ተበዳይ የሆነውን 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክርን ይዞ ወደ ፍትሕ ሚኒስቴር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ቢሮ በመሄድና ኃላፊውን እንደሚያውቀው በማስመሰል በግል ተበዳይ በኩል እምነት እንዲጣልበት መሞከሩን ክሱ ያስረዳል::

እንዲሁም በቦሌ ክፍለ ከተማ 22 አካባቢ ከዚሁ 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክርን ጉዳይ ለማስፈጸሚያ 2 ሚሊየን ብር እንዲያመጣ ከዚህም ውስጥ ቅድሚያ ክፍያ 350 ሺህ ብር እንዲሰጠው መጠየቁ በክሱ ተጠቅሷል::

በዚህ መነሻ፥ የካቲት 21 ቀን 2015 ዓ.ም 42 ሺህ ብር፣ የካቲት 22 ቀን 2015 ዓ.ም 100 ሺህ ብር እንዲሁም የካቲት 24 ቀን 2015 ዓ.ም 40 ሺህ ብር በተለያዩ ሰዎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከፈተ የሒሳብ ቁጥር ገቢ እንዲደረግለት ማስደረጉም ነው የተመለከተው::

በመቀጠልም የበለጠ በሐሰት ታማኝነት ለማግኘት በማሰብ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አካባቢ የግል ተበዳይ 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክርን ይዞ በመሔድ ከፍተኛ ኃላፊዎችን እንደሚያውቅ ለማስመሰል ጥረት አድርጓልም ነው የተባለው::

ሠነዶችን በዐቃቤ ሕግ ቢሮ እንዳስገባ በማስመሰል ጉዳዩ ለውሳኔ እንዲቀርብ ተጨማሪ 150 ሺህ ብር በመጠየቅ መጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 ደሳለኝ ሆቴል 1ኛ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ማለትም የግል ተበዳይ ገንዘቡን ይዞ እንዲመጣ በመንገር 80 ሺህ ብር በቼክ 50 ሺህ ብር በጥሬ ገንዘብ ከግል ተበዳይ ተቀብሎ ሊያመልጥ ሲል በቁጥጥር ስር መዋሉ በክሱ ተገልጿል።

በዚህም የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 29 (1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በግል ተሰሚነት መንገድ የሙስና ወንጀል መፈጸም በሚል ተከሷል።

ተከሳሹ ክሱ ከደረሰው በኋላ በጠበቃው አማካኝነት የዋስትና መብቱ እንዲጠበቅ ባቀረቡት ጥያቄ ላይ ከከሳሽ ዐቃቤ ሕግ ጋር ክርክር ተደርጎበት ብይን ለመስጠት ተለዋጭ ቀጠሮው ተሰጦታል።

በተያያዘ ሌላ መረጃ 4 ሺህ 392 ካሬ ሜትር ይዞታን ያለአግባብ ለግለሰቦች እንዲሰጥ በማድረግ ከ132 ሚሊየን ብር በላይ ጉዳት በማድረስ ወንጀል የተጠረጠሩ 48 ተከሳሾች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተ። ክሱ የተመሰረተው በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሙስና ወንጀል ችሎት ነው።

የፍትኅ ሚኒስቴር የሙስና ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዐቃቤ ሕግ በ48 ተከሳሶች ላይ የተሳትፎ ደረጃቸውን ጠቅሶ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መስርቷል።

ከተከሳሾች መካከል የየካ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር የሰነድ አጣሪ የሕግ ባለሙያ 1ኛ ተከሳሽ አማረ ሞገስ መንግስቱ፣ 2ኛ ተከሳሽ የክፍለ ከተማው የካሳ ግምትና ምትክ ባለሙያ ቢኒያም ደነቀ እና 4ኛ ተከሳሽ የክፍለ ከተማው የመሬት አስተዳደር የካሳ አፊሰር ምስጋናው ማሰቦ ይገኙበታል።

ከ1ኛ እስከ 27 ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሶች በየካ ክፍለ ከተማ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተመድበው ሲሰሩ የነበሩ ሲሆን፥ ከ28 እስከ 36ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች ደግሞ የአርሶ አደር ኮሚቴ ሳይሆኑ የአርሶ አደር ኮሚቴ ነን በሚል በወረዳ 10 እና ወረዳ 14 በተለያዩ ቦታዎች ሲንቀሳቀሱ የቆዩ ናቸው ተብሏል::

ከ37ኛ እስከ 48ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾችን በአካባቢው ነዋሪ ሳይሆኑ ነዋሪ ነን በማለት ሀሰተኛ ቃለ ጉባዔ ማቅረባቸው በክሱ ተጠቅሷል።

በአጠቃላይ ከጣፎ እስከ ድንበሯ በሚዘረጋ የከባድ የኤሌክትሪክ መሥመር ዝርጋታ ፕሮጀክት ምክንያት ክፍለ ከተማው የልማት ተነሺዎችን እያስተያናገደ በነበረበት ወቅት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የክፍለ ከተማው ሠራተኛ ናቸው የተባሉ ከ1ኛ እስከ 27 ኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱ ተከሳሾች በህገወጥ መልኩ12 ሚሊየን 882 ሺህ 918 ብር ከ82 ሳንቲም የካሳ ክፍያ እንዲዘጋጅ አድርገዋል ሲል ዐቃቤ ሕግ በክሱ አመላክቷል።

በዚህም የልማት ተነሺ ላልሆኑ 10 ግለሰቦች የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ናቸው በሚል ለያንዳንዳቸው 500 ካሬ ሜትር ይዞታ መብት እንዲፈጠርላቸው በማድረግ ጠቅላላ ወቅታዊ የጨረታ ዋጋው 132 ሚሊየን 37 ሺህ 460 ብር ከ82 ሳንቲም የሆነ 4 ሺህ 392 ካሬ ሜትር ይዞታን በሕገ-ወጥ መንገድ በምትክነት እንዲወሰድ በማድረግ በዋና ወንጀል አድራጊነት እና በልዩ ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ሥልጣንን ያለ አግባብ በመገልገል ከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰዋል::

ከተከሳሾች መካከል 2ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ብቻ ችሎት ቀርበው ክሱ እንዲደርሳቸው የተደረገ ሲሆን፥ በችሎቱ ዳኞች ማንነታቸውን የመለየትና የመመዝገብ ሥራ ተከናውኗል።

ከቀሪ ተከሳሾች መካከል በሌላ የሙስና መዝገብ የተከሰሱና ቀደም ሲል በጊዜ ቀጠሮ ችሎት በዋስ የተፈቱትን ተከሳሾች ጨምሮ 46 ተከሳሾችን የአዲስ አበባ ፖሊስ በቀጣይ ቀጠሮ እንዲያቀርባቸው ታዟል።

በተጨማሪም ሀሰተኛ የወራሽነት ሰነዶችን በማቅረብ ከ10 ሚሊየን ብር በላይ ገንዘብ ሊቀበሉ ሲሉ ተይዘዋል በተባሉ ግለሰቦች ላይ የአታላይነት የሙስና ወንጀል ክስ ተመሰረተባቸው። ተከሳሾቹ መቶ አለቃ አዲስ አልቱ እና ሌተናል ኮሎኔል ሰለሞን አጥናፉ የሚባሉ ሲሆን፥ ክሱ የቀረበውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ የሙስና ጉዳዮች ወንጀል ችሎት ነው::

1ኛ ተከሳሽ ወራሽ ነኝ በሚል የማጭበርበሪያ ስልት በመጠቀም የግል ተበዳይ በሞት እንደተለዩ የሚገልጽ ሀሰተኛ የሞት የምስክር ወረቀት ማዘጋጀቱ በክሱ ተመላክቷል:: በተጨማሪም በስሙ የተዘጋጀ ሀሰተኛ የፍርድቤት የወራሽነት ምስክር ወረቀት ማቅረቡ ነው በክሱ የተብራራው።

ባለቤትነቱ የግል ተበዳይ ወ/ሮ እልፍነሽ ኃይሉ የሆነ አቢሲኒያ ባንክ ቦሌ ኤርፖርት ቅርጫፍ የተከፈተ የቁጠባ ሒሳብ ውስጥ የሚገኝ 10 ሚሊየን 210 ሺህ 669 ብር ከ11 ሳንቲም ለመውሰድ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ ከተማ የባንኩ ሳሪስ ቅርጫፍ ሀሰተኛ የወራሽነት ሰነዶችን አዘጋጅተው በመጋቢት 13 ቀን 2015 ዓ.ም ማቅረባቸው በክሱ ተዘርዝሯል።

ሁለተኛ ተከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ስም የተዘጋጁ ሀሰተኛ የወራሽነት ሰነዶችን በጋራ በመሆን ለባንክ ካቀረቡ በኋላ ትክክለኛ ሰነድ ነው በማለት በፍጥነት ጉዳዩ እንዲፈጸም እና ባንኩ የተሳሳተ እምነት አድሮበት ህገ ወጥ ክፍያ እንዲከፍል ጫና መፍጠሩ በክሱ ተካቷል።

ተከሳሾቹ በዚህ መልኩ ገንዘቡን በሀሰተኛ የወራሽነት ማስረጃ አቅርበው ገንዘቡን ለመውሰድ ሲሉ መያዛቸውም ነው የተጠቀሰው።

በዚህም፥ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 ንዑስ ቁጥር 1( ሀ)ና ለ እንዲሁም የሙስና አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 23 ንዑስ ቁጥር 1( ሀ)፣ ንዑስ ቁጥር 2 (ሀ) እና ንዑስ ቁጥር 3 ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በህዝብ አስተዳደር ወይም በህዝብ አገልግሎት ላይ በሚፈጸም ከባድ አታላይነት የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል።

ተከሳሾቹ ችሎት ቀርበው ክሱ የተነበበላቸው ሲሆን፥ የክስ መቃወሚያ ካላቸው ለመጠባበቅ ለግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ መሰጠቱ ተመላክቷል።

# ኪነ-ጥበብ

ከፈጣሪ በታች ህሊና ዳኛ ነው!

## ከፈጣሪ በታች ህሊና ዳኛ ነው!

አስራ ሁለቱን የስነ-ምግባር መርህ፣ መተርጎም አትርሳ በየዕለት ህይወትህ፤

ሙስናን መዋጊያ አጥፊ ነው መሳሪያ፣ ትውልድን መቅረጫ እንድንሆን አርዓያ፤

ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ግልፅነት፣ ሃቀኝነት እና ሚስጥር ጠባቂነት፤

የህዝብን ጥቅም ሁሌም በማስቀደም፣ የተሰጠንን ስልጣን በአግባቡ በመጠቀም፤

አለማዳላት፣ ተጠያቂነትን፣ ህግን በማስከበር፣ አርዐያ በመሆን፤

ህዝብን እናገልግል ለዜጋ እንወግን፡፡

በተለምዶ አንብበን ካደረግነው ፊደል፣ ግድግዳ ማሞቂያ ከመሰለን ስዕል፤

ስህተት እንዳይገጥመን ወገኔ እናስተውል፡፡

እንደጦር ታጥቀን፣ እንደልብስ ለብሰን፣ አገር አውዳሚውን ሙስናን እንኮንን፤

ትውልድን እናድን መርሆቹን ኖረን፡፡

ፊት አይተን ሳንፈርድ ፍትህ ሳናዛባ፣ በገንዘብ በጥቅም ሳንሆን ተላላ፤

ቃላችንን እንጠብቅ አደራ እንወጣ፣ የዘሩትን ማጨድ አለና በኋላ፡፡

በተሰጠን ጊዜ ባለብን አደራ፣ ታማኞች እንሁን በትጋት እንስራ፡፡

በስነ-ምግባር የታነፀን እውነተኛ ዜጋን፣ ሙስናን ሚፀየፍ ውሸት ሌብነትን፤

ትውልድን እንፍጠር አርአያ እንሁን፡፡

እኛው ካበላሸን፣ እኛው ሌባ ከሆን፣ እረ ማነው እስቲ ተተኪ የሚሆነን፤

ጓዳችን ይፈተሽ እራሳችን እንይ፣ በማንም ባንታይ ይፍረድ ህሊናችን፤

ልክ ነህ ልክ ነሽ ይበለን ይንገረን፣ አሊያም እንዳጠፋን ይቆጥቆጥ ይውቀሰን፡፡

እንዳልሰማ አንለፍ እስቲ እናድምጠው፣ ከፈጣሪ በታች ህሊና ዳኛ ነው፡፡

ታሪኳ ግርማ

# መልካም ዜጋ

## ታማኝነት በገቢ መጠን አይለካም!

ከድር ጀማል

ታማኝ፣ እውነተኛ፣ እምነት የሚጣልበት መሆን፣ የተሰጠን ሥራ በተባለው ጊዜና በትክክለኛው መንገድ መስራትና ማጠናቀቅ፣ ከሌሎች ለመማር ዝግጁ መሆን፣ የራስ ብቃትና ችሎታን የማሳደግ ጥረትና ትጋትና የሌሎች ችሎታ ለማዳበር ቅን መሆን አንድ የመንግስት ሠራተኛ ሊላበሳቸው የሚገቡ መሠረታዊ የሥራ መልካም ባህርያት ናቸው።

እንደሚታወቀው በመንግስት የተሰጠን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ አለመወጣት፥ ትንሽ መስራት፣ ብዙውን በቀልድና በዋዛ ፈዛዛ ማሳለፍ፣ በሥራ ላይ የሚገጥሙ ችግሮችን ለመፍታት ምንም መነሳሳትን አለማሳየት፣ እምነት ማጉደል፣ ማጭበርበር፣ መስረቅ ለሥራ የሚገባውን ክብርና ፍቅር አለመስጠትና ሥራን ከፍና ዝቅ አድርጎ ማየት በተንሰራፋበት በዚህ ወቅት ታማኝነት በተግባር የሚያሳዩ ሰዎችን ማግኘት ብርቅ እየሆነ መጥቷል።

የሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነት ባለማጉደል ታማኝነትን በተግባር ካስመሰከሩ የመንግስት ሠራተኞች አንዷ ወ/ሮ በቀሉ ሙለታ ናቸው። ወ/ሮ በቀሉ በኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአትክልትና ፍራፍሬ ንግድ ሥራ ዘርፍ ዋና መ/ቤት የቢሮ ውበትና ረዳት ፀሐፊ የሥራ መደብ ላይ ብር 2,000 (ሁለት ሺህ ብር) ወራዊ ደመወዝ እየተከፈላቸው ከስድስት ዓመት በላይ ያህል በማገልገል ላይ የሚገኙ ሲሆኑ፥ በመልካም ሥነምግባራቸው የተመሰገኑና ከሌሎች የሥራ ባለደረቦቻቸው ጋር መልካም የሥራ ግንኙነት በመፍጠር ለሌሎች አርዓያ የሆኑ ሠራተኛ ናቸው።

በአንድ ወቅት የሥራ ሥነምግባራቸውን የሚፈታተን አጋጣሚ ተፈጠረ። ይህውም መደበኛ ሥራቸውን ማለትም የቢሮ ውበት ሥራ በሚሰሩበት አካባቢ በሚገኝ አግዳሚ ወንበር /የእንግዳ ማረፊያ/ ላይ ባለቤቱ የማይታወቅ ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል) ወድቆ ያገኛሉ። የንብረቱ ባለቤት ማን እንደሆነ ለማረጋገጥ ዙሪያውን ቢመለከቱም በአካባቢው ምንም ሰው ሊያገኙ አልቻሉም። "የዚህ ንብረት ባለቤት ማን ሊሆን ይችላል?" የሚል ጥያቄ በአዕምሯቸው አንቃጨለ። ይህ ንብረት የውስጥ ሠራተኛ ወይም የውጭ ደንበኛ ሊሆን ስለሚችል ሞባይል ጠፍቶብኛል ብሎ የሚመጣ ሰው እስኪገኝ ድረስ ስልኩን በእጃቸው ይዘው ይጠባበቁ ጀመር።

ሆኖም "ሞባይል ጠፍቶብኛል" ብሎ የሚጠይቅ የውስጥም ሆነ የውጭ ተገልጋይ ባለማግኘታቸው የተነሳ ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ። እንደ አንድ አማራጭ የመፍትሔ እርምጃ አድርገው የወሰዱት በድርጅቱ ውስጥ ንብረት ወድቆ ወይም ጠፍቶ ከተገኘ በቀጥታ የዘርፉን ሠራተኞችን አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት ለሚመራው የሰው ሀብት መምሪያ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይወስናሉ።

ከዚያም ወድቆ የተገኘውን ሞባይሉን ይዘው፣ "ይህ ንብረት የኔ አይደለም፤ በምሰራበት አካባቢ ወድቆ አግኝቸዋለሁ። የንብረቱ ባለቤት መጥቶ ይጠይቃል ብዬ ብጠብቅም ሊመጣ አልቻለም። የንብረት ባለቤት ማን እንደሆነ ማወቅ አልቻልኩም፤ ስለዚህ እናንተ ባለቤቱን ፈልጋቹሁ አስረክቡልኝ፣አደራ" በማለት ለድርጅቱ ከፍተኛ የሰው ኃብት አስተዳደር ባለሙያ ሞባይሉን ያስረክባሉ።

የዘርፉ ሰው ሀብት መምሪያ ባለሙያም፤ "እስካሁን ሞባይል ጠፍቶብኛል ብሎ ያመለከተ የውስጥ ሠራተኛ የለም። ለማንኛውም የንብረቱን ባለቤት ነኝ ብሎ ማስረጃ የሚያቀርብ ሰው እስኪመጣ ድረስ ሞባይሉን በጥንቃቄ እናስቀምጣለን" በማለት

**ሰዎችን መመዘን ያለባቸው በሚናገሩት ንግግር ሳይሆን በሚፈጽሙት ተግባር መሆን አለበት። ምክንያቱም የሰው ልጅ ትልቁ መለኪያ መሆን ያለበት የገባውን ቃል በታማኝነት ጠብቆ መፈፀም ሲችል ብቻ ነው**



ንብረቱን ከወ/ሮ በቀሉ ሙለታ ይረከባል። ሆኖም የንብረቱ ባለቤት ነኝ የሚል ግለሰብ እስኪመጣ ለተወሰኑ ቀናት በትዕግስት ቢጠበቅም፤ "ሞባይል ጠፍቶብኛል" ብሎ የቀረበ ሰው ባለመኖሩ ሞባይሉ የተገኘበት መንገድ በዝርዝር ተገልጾ ለዘርፉ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል መካከለኛ ባለሙያ እንዲረከቡት ይደረጋል።

የሥነምግባር ባለሙያዋ ንብረቱን ተረክበው ከተለያዩ የውስጥ ሠራተኞች መረጃዎችን የማሰባሰብ ሥራ መሥራት ጀመሩ። ጉዳዩ በመጣራት ላይ እያለ አንድ የዘርፉ የውስጥ ሠራተኛ በመስሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሞባይል እንደጠፋበት ሪፖርት ይቀርባል።

ይህ የንብረቱ ባለቤት ነኝ የሚል ግለሰብ፣ ሞባይል መቼ እንደጠፋበት? የት ቦታ እንደጠፋበት? የሞባይሉ የቀለም ዓይነት ምን እንደሆነ? ሞዴሉ እና ሌሎች ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ይደረጋል። ተገቢ የሆነ የማጣራት ሥራ ከተሰራ በኃላ የንብረቱ ባለቤትነት በማስረጃ በመረጋገጡ ሞባይሉ በዘርፉ በጀማሪ አካውንታንት የሥራ መደብ ላይ ለሚገኙት ባለሙያ ማስረከብ ተችሏል።

እዚህ ጋር በአግባቡ መረዳት የምንችለው በተለያየ የሥራ ተግባርና ኃላፊነት ደረጃ ብንቀመጥም በመንግሥትና በህዝብ የተሰጠን አደራ በኃላፊነትና በታማኝነት ለመወጣት የሥራ ሥነምግባር የሚጠይቀውን የሞራል ስታንደርድ ጠብቆ መገኘት እንጂ የገቢ መጠን ከፍና ዝቅ በማለት የሚለካ አለመሆኑን ነው።

በአጠቃላይ ወ/ሮ በቀሉ ሙለታ የመልካም ሥነምግባር መርሆ የሆነው ታማኝነትን በተግባር በማረጋገጣቸው በኮርፖሬሽን ደረጃ የገንዘብ ሽልማትና የዕውቅና የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሲሆን፥ የሚሰሩበት የሥራ ዘርፉም በመልካም ሥነምግባር አርዓያ ሆነው በመገኘታቸው ከፍተኛ ምስጋናንና ክብር እንዲሁም ከንብረቱ ባለቤት የምስጋና ድብዳቤ የተጻፈላቸው ሲሆን፥ በሥራ አጋሮቻቸው ክብርና ምስጋና አግኝተዋል። ከዚህ የበለጠ ምን ደስታና የሥራ እርካታ አለ ትላላችሁ?